3. ኢየሱስ ተዓምራት እንደ ሰራ ቁርዓን ይመሰክራል /ሱራ 3፡49፣ 5፡110-115 ወደ እስራኤልም ልጆች መልክተኛ ያደርገዋል /ይላልም/ እኔ ከጌታዬ ዘንድ በታምር መጣሁላችሁ:: እኔ ለናንተ በጭቃ እንደ ወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ በርሱም እተነፍስበታለሁ በአላህም ፈቃድ ወፍ ይሆናል:: በአላህ ፈቃድ እውር ኾኖ የተወለደን ለምጸኛንም አድናለሁ ሙታንንም አስነሳለሁ:: የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታስቡትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ የምታምኑ እንደኾናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ በእርግጥ ታምር አለበት::

አላህ በሚል ጊዜ/ የዋልኩላችሁ ጸጋዬን አስታውስ በሕፃናትና በከፈኒሳነት /በገብርኤል/ ባበረታሁህ ጊዜ ጽሕፈትንና ጥበብንም ተውራትንና ኢንጂልንም ባስተማርኩህ ጊዜ ከጭቃም የወፍ ቅርጽ ብጤ በፈቃዴ በምትሠራና በውስጧ በምትነፋ በፈቃዴ ወፍ በምትኾን ጊዜ ዕውርም ኾኖ የተወለደንና ለምጸምንም በፈቃዴ በምታሽር ጊዜ ሙታንንም በፈቃዴ /ከመቃብራቸው/ በምትወጣ ጊዜ የእስራኤልንም ልጆች በተአምራት በመጣህባቸውና ከነሱ እነዚያ ይህ ግልጽ ድግምት እንጂ ሌላ አይደለም ባሉ ጊዜ /ሊገድሉህ ሲያስቡህ/ ከአንተ ላይ በከለከለሁህም ጊዜ / ያደረኩልህን ውለታ አስታውስ /:: ወደ ሐዋርያትም በኔና በመልክተኛዬ እመኑ በማለት ባዘዝኩበት ጊዜ አስታውስ/ አመንን ሙስልሞች መኾናችንን መስክር አሉ:: ሐዋርያት የማርያም ልጅ ዒሳ ሆይ ጌታህ በኛ ላይ ከሰማይ ማእድን ሊያወርድልን ይችላልን ባሉ ጊዜ /አስታውስ /ምእመናን እንደ ኾናችሁ አላህን ፍሩ አላቸው:: ከርሷ ልንበላ ልቦቻችንም ሊረኩ እውነት ያልከንም መኾንህን ልናውቅና በርሷም ላይ ከመስካሪዎች ልንኾን እንፈልጋለን አሉ:: የማርያም ልጅ ዒሳ አለ ጌታችን አላህ ሆይ! ለኛ ለመጀመሪያዎችንና ለመጨረሻዎችን በአል /መደሰቻ/

የምኾንን ከአንተም ተአምር የኾነችን ማእድ ከሰማይ በኛ ላይ አውርድ ስጠንም አንተ ከሰጪዎች ሁሉ በላጭ ነህና::

አላህ:- እኔ /ማእድዋን/ በናንተ ላይ አውራጅዋ ነኝ በኋላ ከእናንተ የሚክድ ሰው ከዓለማት አንድንም የማልቀጣውን ቅጣት እቀጣዋለሁ አለ:: /ሱራ 5፥110-115/

መሀመድ በቁርዓን ተዓምር ሰርቶአል ተብሎ አንድ ጊዜም አልተፃፈም ሐዋሪያቶች ሙስሊሞች ነን ብለው መስክረዋል ይላል ቁርዓን ሐዋሪያቶች ከጌታ ጋር የተገናኙበት ጊዜ በ30ዓ.ም. ቢሆን የወንጌል አደራ ከጌታ እጅ የተቀበሉት ደግሞ በ33ዓ.ም. አጋማሽ ላይ ነው:: በ96 ዓ.ም. አካባቢ ሁሉም ምድራዊ ሩጫቸውን ጨርሰው አልፈዋል:: እስልምና የመጣው በነብዩ መሀመድ አማካይነት በ610 ዓ.ም. ነው::

4. ወደ ሰማይ ማረጉ ከኢየሱስ ሌላ በቁርዓን ማንም አረገ አይልም:: ይልቁንስ አላህ ወደርሱ አነሳው አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው:: /ሱራ 4፥158/
5. በህፃንነቱ መናገሩ በኢንጅል ያልተፃፈ በቁርዓን ተፅፎአል /ሱራ 19፥29-30/
6. ፈጣሪነቱ የሕይወት እስትንፋስ መስጠቱ ለአምላክ ብቻ የተሰጠ ችሎታ ሆኖ ሳለ ቁርዓን ኢየሱስ ፈጠረ ይላል:: እነዚህን ሁሉ መስራቱ ሁሉን ቻይ አምላክ መሆኑን ከላይ ያየናቸው የቁርዓን ክፍሎች ያረጋግጣሉ::

እግዚአብሔር በቀድሞ ዘመናት በተለያየ መንገድ በነቢያት አማካይነት ለአባቶቻችን ብዙ ጊዜ ተናግሮ ነበር::አሁን ግን በእነዚህ በመጨረሻው ቀኖች ሁሉን ነገር ወራሽ ባደረገው በልጁ አማካይነት ለእኛ ተናገረን ዓለምንም ሁሉ የፈጠረበት በእርሱ ነው:: እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነፀብራቅ ነው እርሱ በባህሪዩ ከእግዚአብሔር

ጋር ፍፁም ትክክል ነው ሥልጣን ባለው ቃሉ ዓለምን ሁሉ ደግፎ ይዞአል:: ሰዎችንም ከኃጢያት ከነፃ በኋላ በሰማይ በሀያሉ እግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል:: ዕብ. 1፥1-3

የኢየሱስ መወለድ ቁርዓን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንሽ ለወጥ ባለ መልኩ አስቀምጦታል:: መርየም ከቤተሰቧ ወደ ምስራቃዊ ሥፍራ በተለየች ጊዜ /የሽውን ታሪኳን/ አውሳ:: ከነርሱም መጋረጃን አደረገች መንፈሳችንንም /ጂብሪልን/ ወደርሷ ላክን ለርሷም ትክክለኛ ሰው ሆኖ ተመሰለላት:: እኔ ከአንተ አልረሕማን እጠብቃለሁ ጌታህን ፈሪ እንደ ኾንክ /አትቅረበኝ/ አለች::

እኔ ንጹሕን ልጅ ለአንች ልስጥሽ የጌታህ መልክተኛ ነኝ አላት:: /በጋብቻ/ ሰው ያልነካኝ ኾኜ አመንዝራም ሳልኾን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል:: ጌታህ እርሱ በእኔ ላይ ገር ነው ለሰዎችም ታምር ከኛም ችሮታ ልናደርገው/ይህንን ሠራን / የተፈረደም ነገር አለ:: ወዲያውኑም አረገዘችው በርሱም /በሆድዋ ይዛው/ ወደ ሩቅ ስፍራ ገለል አለች:: ምጡም ወደ ዘንባባይቱ ግንድ አስጠጋት ዋ! ምኞቴ ምነው ከዚህ በፊት በምትኩ ተረስቼም የቀረሁ በኾንኩ አለች:: ከበታቿም እንዲህ ሲል ጠራት አትዘኝ ጌታሽ ወንዝ በእርግጥ አድርጓል::

የዘምባባይቱንም ግንድ ወንዳንች ውዝውዢት ባንቺ ላይ የበሰለን የተምር እሸት ታረግፍልሻለችና:: ብይም ጠጭም ተደሰችም ከሰዎችም አንድን ቢታይ እኔ ለአልረሕማን ዝምታን ተስያለሁ ዛሬም ሰውን በፍጹም አላነጋግርም በይ::

በእርሱም የተሸከመቺው ኾና ወደ ዘመዶችዋ መጣች መርየም ሆይ ከባድን ነገር በእርግጥ ሠራሽ አሏት:: የሃሩን እህት ሆይ አባትሽ መጥፎ ሰው አልነበረም እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም አሉዋት:: ወደርሱም ጠቀሰች በአንቀልባ ያለን ሕፃን እንዴት እናናግራለን አሉ::/ሕፃኑም/ አለ እኔ ለአላህ ባሪያ ነኝ መጽሐፍም ሰጥቶኛል

ነቢይም አድርጎኛል፡፡ በየትም ስፍራ ብሾን ብሩክ አድርጎኛል በሕይወትም እስከአለሁ ሶላትን በመስገድ ዘካንም በመስጠት አዞኛል፡፡ ሱራ 19፥16-31

ይህ ክፍል ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ በተዓምር መፀነሱ ማርያም ከአካባቢው ራቅ ብላ በዘንባባ ግንድ መውለዷ እንደ ወለደች ስለ ተራበች አላህ የዘንባባውን ግንድ ወዘውዥው ባላት ጊዜ የዘንባባው ግንድ ይዛ ስትወዘውዘው የበሰለ ዘንባባ ተንጠባጠበላት የማርያም ዘመዶች ልጅ አዝላ በማየታቸው አባትሽና እናትሽ የተቀደሱ ነበሩ አንቺ መጥፎ ተግባር ፈጸምሽ አሉአት በዚህ ጊዜ ዒሳ እንደ ታዘለ በመናገሩ ልጅ መውለዷ የአላህ ፈቃድ መሆኑን አውቀዋል፡፡

እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ሳለች ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች፡፡ እጮኛዋ ዮሴፍ ደግሰው ስለነበረ ማርያምን በሰው ፊት ሊያጋልጣት አልፈለገም ስለዚህ በስውር ሊተዋት አሰበ፡፡ ይህን ነገር ሲያስብ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም ተገልጦለት እንዲህ አለው የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ እጮኛህ ማርያም የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ ስለሆነ እርሷን ወደ ቤትህ ለመውሰድ አትፍራ፡፡ እርሷ ወንድ ልጅ ትወልዳለች እርሱ ህዝቡን ከኃጢያታቸው ስለሚያድን ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ ይህን ሁሉ የሆነው እግዚአብሔር በነቢይ እንድህ ስል የተናገረው እንድፈፀም ነው፡፡ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ተብሎ ይጠራል፡፡

አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነው ማለት ነው፡፡ ነቢያቶች በመንፈስ ተረድተው ጌታ እንደ ሚወለድ ተንብየዋል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሌሎች የሃይማኖት መሪዎች አይደለም ዓለምን የማዳን ተልእኮ ይዞ ነው የመጣው፡፡

## 1. ነቢያትና ሐዋሪያት ኢየሱስ ማን ነው ለሚለው ጥያቄ መልስ ሰጥተዋል

◆ አንደኛ የሚወለድበትን ከተማ ለይተው ተናግረዋል።

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል አንቺ በኤፍራታ ምድር የምትገኚ ቤተልሔም ሆይ ምንም እንኳን አንቺ ከይሁዳ ከተሞች ያነስሽ ብትሆኚም አወጣጡ ከጥንት ዘመናት በፊት የሆነ የእስራኤል መሪ ከአንቺ ይወጣል"ሚክ. 5፥2

ነገስታት የሚወለዱት በኢሩሳሌም ነው። የዳዊት የዘር ሀረግ መነሻው ከዚሁ ከኢየሩሳሌም ነው። ነብዩ ሚክያስ የሚቃረን ትንቢት ነው የተናገረው። ሄሮድስ የካህናት አለቆችና የሕዝቡን የህግ መምህራን አስጠርቶ መሲሕ የሚወለደው የት ነው? ሲል ጠየቃቸው። እነርሱም እንዲህ ብለው መለሱለት "መሲህ የሚወለደው በይሁዳ ክፍለ ሀገር በቤቴልሔም ከተማ ነው" ። ምክንያቱም በነቢዩ እንዲህ የሚል ተጽፎአል። "በይሁዳ ከተማ ሀገር የሚትገኚ አንቺ ቤቴልሔም ሆይ ከይሁዳ ሀገር ዋና ዋና ከተሞች ከቶ አታንሽም ምክንያቱም ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መሪ ከአንቺ ይወጣል" ማቴ. 2፥4-6

◆ ሁለተኛ እግዚአብሔር ስለ ኢየሱስ /ዒሳ/ መስክሯል።

ኢየሱስ ተጠምቆ ከውሀ እንደወጣ ወድያውኑ ሰማይ ተከፈተ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርግብ አምሳል ወርዶ በኢየሱስ ላይ ሲያርፍ አየ። በዚያኑ ጊዜ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ። ማቴ. 3፥16-17

◆ ሦስተኛ የእግዚአብሔር መልአክ ስለ ክርስቶስ መስክሯል።

መልአኩም ወደ እርሷ መጥቶ አንቺ ፀጋ የሞላብሽ ሰላም ለአንቺ ይሁን እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው። አንቺ ከሴቶች መሐከል የተባረክሽ ነሽ አላት። እርሷም በመልአኩ አነጋገር ደንግጣ ይህ ምን አይነት ሰላምታ ይሆን ብላ አሰበች። መልአኩም እንዲህ አላት

ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አግኝተሻልና አትፍሪ እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይውአለሽ እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል እግዚአብሔር ልጅም ይባላል ጌታ አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል በእስራኤልም ላይ ለዘላለም ይነግሣል ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም::ሉቃ.1፥28-33

◆ አራተኛ ክርስቶስ ስለ ራሱ መስክሯል::

ከአይሁድ ጋር በሚወያይበት ጊዜ እንዲህ ብሎአል:: አባቴ ሁልጊዜ ይሠራል እኔም እሠራለሁ ሲል መለሰላቸው ይህ አባባል አይሁዳውያን ባለሥልጣኖችን ኢየሱስን እንዲገድሉት ይበልጥ አነሣሣቸው እርሱ ሰንበት በመሻሩ ብቻ ሳይሆን ከእግዚብሔር ጋር ራሱን ስለ አስተካከለ ነው:: ዩሐ. 5፥17-18

◆ አምስተኛ ስለ ክርስቶስ የመጥመቁ ዮሐንስ ምስክርነት

ቀጥሎም ዮሐንስ እንዲህ ሲል መሰከረ መንፈስ ቅዱስ እንደርግብ ከሰማይ ሲወርድና ሲያርፍበት አየሁ እኔ ራሴ አላውቀውም ነበር ነገር ግን በውሀ እንዳጠምቅ የላከኝ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው ሲል ነግሮኛል:: እኔም ይህን አይቻለሁ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እመሰክራለሁ:: ዮሐ. 1፥34

◆ ስድስተኛ የጴጥሮስ በመገለጥ የተሞላ ምስክርነት

ኢየሱስ አስራሁለቱ እናንተም ደግሞ መሄድ ትፈልጋላችሁን አላቸው:: በዚህ ጊዜ ስምዖን ጴጥሮስ እንዲህ ሲል መለሰ:: ጌታ ሆይ ወደ ማን እንሄዳለን አንተ የዘላለም የሕይወት ቃል አለህ እኛስ አምነናል ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ አንተ እንደሆንህ አውቀናል:: ዮሐ 6፥67-69

◆ ሰባተኛ ወንጌላዊ ዩሐንስ ስለ ክርስቶስ የሰጠው የምስክር ቃል

"አባት ልጁን ይወዳል ሁሉንም ነገር በእጁ አስረክቦታል በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖርበታል እንጂ ሕይወትን አያገኝም":: ዮሐ. 3፥35-36

◆ ስምንተኛ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት

ስለ ጌታ የሰጠው ምስክርነት የምስራቹ ቃል የእግዚአብሔር ልጅ በሰብአዊነቱ በኩል ከዳዊት ዘር መወለዱ የሚያበስር ነው:: እንዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅድስናው መንፈስ በኩል በታላቅ ኃይል ከሞት በመነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያበስር ነው:: ሮሜ 1፥3-4

ምናልባት ልጅ የሚለው ቃል በሰብአዊው አእምሮ ግራ ወደ ሚያጋባ ድምዳሜ የሚያደርስ ይሆናል:: አባት የሚለው ቃል በማነፃፀር ከልጅ ቀድሞ የተገኘ ነው በማለት ወልድ ከአብ በኋላ የመጣ ነው ይላሉ:: እዚህ ጋ ልናስብበት የሚገባ ነገር አለ ይኸውም ልጅ የሚለው ቃል ከአባት ጋር እኩል አይደለም ወደ ሚለው ድምዳሜ አያደርሰንም ወይም ከአብ በኋላ የመጣ ነው ማለት አይደለም:: እንዲያውም የእግዚአብሔር ልጅ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ማለት ነው:: ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነን ጥቅስ እንመልከት ኢየሱስ ግን አባቴ ሁልጊዜ ይሠራል እኔም እሠራለሁ ሲል መለሰላቸው::

ይህም አባባል አይሁድ ባለሥልጣናት ኢየሱስን እንዲገድሉት በይበልጥ አነሳሳቸው ምክንያቱም እርሱ ሰንበትን በመሻሩ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር አባቴ ነው በማለቱ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ስለአስተካከለ ነው :: ከአብ ዘንድ ወጥቶ ወደዚህ ዓለም እንደመጣ ከተነገረበት ጊዜ እና ከመጣ በኋላ ነው ልጅ የሚለው ስያሜ ያገኘው::

ክሴት ስለ ተወለደ የልጅ አስተዳደግ ተከትሎ ስለ አደገ ልጅ የሚለው ስም ተሰጥቶታል:: ለመጀመሪያ ጊዜ ልጅ ብለው የጠሩት የብሉይ ኪዳን ነቢያቶች ናቸው::

ንጉሡም እነሆ እግዚአብሔር የሰጠውን ትዕዛዝ አውጃለሁ እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ መዝ. 2፥7 ወንጌላዊ ዮሐንስ የጌታ ወደዚህ ዓለም አመጣጥ እንዲህ ይተርከዋል "ቃል ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ በእኛ አደረ:: አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን" ዮሐ. 1፥14

ጌታ የሰውን ልጅ ማን ይሉታል ብሎ ደቀመዛሙርቱን ጠየቀ:: ዛሬ ክርስቶስን በተመለከተ ጥያቄዎችን መጠየቅ ተገቢ ነው:: ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ ታምናለህ ምን ማስረጃ አለህ? ሰዎች ኢየሱስ አምላክ አይደለም ፍጡር ነው ወይም ነቢይ ነው ብለው ያምናሉ ያስተምራሉ:: ለመሆኑ በምን ምክንያት ነው ሌሎች ሰዎች በክርስቶስ መለኮትነት የሚያምኑት? እስቲ ጥያቄዎቹን አብረን እንመልሳቸው::

### 3. ትንቢታዊ ማስረጃ

እነሆ ህፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና እርሱም መሪ ይሆናል:: ስሙም ድንቅ መካሪ ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ይባላል:: ኢሳ. 9፥6

እንግዲህ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል:: እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነው ኢሳ. 7፥14

እግዚአብሔር ለጌታዬ /ለመሲሁ/ ጠላቶችን በሥልጣንህ ሥር እስከማደርግልህ ድረስ በቀኝ ተቀመጥ አለው መዝ. 110፥1 ይህ ክፍል የአብና የወልድ ዘላለማዊ ግንኙነት ጥልቅ ምስጢር የያዘ ነው::

ኢየሱስ ከአብራሃም በፊት ነበር ኢየሱስ እውነት እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው::ዮሐ.8፥58

እኔ የሚለው የጌታ ኢየሱስ አገላለፅ እግዚአብሔር ለሙሴ ራሱን ከገለጸበት ጋር ተመሳሳይነት አለው::

ሙሴም እኔ ወደ እስራኤል ሕዝብ ሄጄ የቀድሞ የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ልኮኛል በምልበት ጊዜ እነርሱ ስሙ ማን ነው ብለው ብጠይቁ ምን እመልስላቸዋለሁ? አለ እግዚአብሔርም እንዲህ አለው:: እኔ ያለሁና የምኖር ነኝ ስለዚህም ያለና የሚኖር ወደ እናንተ ልኮኛል በላቸው:: ዘፀ. 3፥13-14

## 4. በሁሉም ሥፍራ ይገኛል

ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡበት ሥፍራ በመካከላቸው እገኛለሁ ማቴ. 18፥20 ጌታ ኢየሱስ ከሰማይ ነው የመጣው ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም ዮሐ. 3፥13 ኢሳ /ኢየሱስ / መጀመሪያና መጨረሻ የለውም:: ያለውና የነበረው የሚያመጣውም ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር አምላክ አልፋና አሜጋ የመጀመሪያውና የመጨረሻው እኔ ነኝ ይላል ዮሐ. 1፥8

መለኮታዊ ሥራው ማስረጃ ነው ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጠረ ከተፈጠረው ሁሉ አንድም ነገር ያለ እርሱ የተፈጠረ የለም በእርሱ ሕይወት ነበረች ይህች ሕይወት የሰዎች ብርሃን ነበረች ዮሐ. 1፥3-4

በሰማይና በምድር ያሉት የሚታዩትና የማይታዩት የሰማይ ኃይሎች እና ገዥዎች አለቆችና ባለሥልጣኖች ሁሉ የተፈጠሩት በእርሱ ነው ቆላ. 1፥16

ሙታን ማስነሳቱ ጌታ ባያት ጊዜ ራራላትና አይዞሽ አታልቅሽ አላት ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ፊት ራመድ ብሎ ቃሬዛውን ነካ

ቃሬዛውን የተሸከሙ ሰዎች ቆሙ ኢየሱስም አንተ ወጣት ተነስ እልሃለሁ አለው የሞተውም ቀና ብሎ ተቀመጠና መናገር ጀመረ ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ለእናትየዋ ልጅሽ ብሎ ሰጣት።
ሉቃ. 7፥13-15

በዓለም ሊፈርድ ይመጣል። " ቀጥሎ ኢየሱስ እንዲህ አለ የሰው ልጅ በመልአክቱ ሁሉ ታጅቦ በክብር ሲመጣ በክብር ዙፋን ላይ ይቀመጣል ሕዝቦች ሁሉ በፍቱ ይሰበሰባሉ እረኛ በጐችን ከፍየሎች እንደ ሚለይ እርሱም ሕዝቦችን ይለያል"።ማቴ.25፥31-32 አምልኮ ተቀብሎአል ወደ ቤትም ገብተው ህፃኑ ከእናቱ ጋር ሆኖ አዩት ተንበርክከውም ሰገዱለት ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው የወርቅ የእጣንና የከርቤ ስጦታ አቀረቡለት ማቴ. 2፥11 የኃጢአት ይቅርታ መስጠቱ ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን አንተ ልጅ ኃጢአትህ ተደምስሶልሀል አለው ከሙሴ ህግ መምህራን አንዳንዶች በዚያ ዙሪያ ተቀምጠው ነበር እነርሱም በልባቸው እንዲህ አሉ። ይህ ሰው ለምን እንዲህ ያለ ስድብ በእግዚአብሔር ላይ ይናገራል ። ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአትን ሊደመስስ የሚችል ማን ነው? ወዲያውኑ ኢየሱስ የልባቸውን ሀሳብ አውቆ እንዲህ አላቸው ስለ ምን በልባችሁ ይህን ታስባላችሁ? ሽባውን ኃጢአትህ ተደምስሶአልሀል ከማለትና ተነስተህ አልጋህን ተሸከምና ሂድ ከማለት የትኛው ይቀላል። ነገር ግን የሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ለመደምሰስ ሥልጣን ያለው መሆኑን እንድታውቁ ብሎ ሽባውን ተነስ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ እልሃለሁ አለው።ሽባውም ወዲያውኑ ተነሣና አልጋውን ተሸክሞ በሰዎቹ ሁሉ ፊት ወጣ። ስለዚህም ሰዎቹ ሁሉ ተደንቀው እንዲህ ያለ ነገር ከቶ አይተን አናውቅም እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ማር. 2፥5-12

የዘላለም ሕይወት መስጠት መቻሉ "በጐቼ ድምጼን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ"::እነርሱም ይከተሉኛል እኔ የዘለላም ሕይወት እሰጣችኋለሁ ስለዚህ ከቶ አይጠፉም ከእኔ እጅ ማንም ነጥቆ አይወስዳቸውም ዮሐ. 14፥18-11

ፊልጾስም ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው ኢየሱስም እንዲህ ስል መለሰለት ፊሊጾስ ሆይ ይህን ያህል ጊዜ ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔም ያየ አብን አይቶአል ታዲያ አንተ አብን አሳየን እንዴት ትላለህ? እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? ለእናንተ የምናገረው ቃል በራሴ ሥልጣን አይደለም ነገር ግን ሥራውን ሁሉ የሚሠራው በእኔ የሚኖረው አብ ነው እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑ አለበለዚያ በሥራዎቼ ምክንያት እመኑኝ::

ከአብ ጋር እኩል የመለኮት ባሕርይ አለው ፊል. 2፥6-8 እርሱ የመለኮት ባሕርይ አለው ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሚያደርገውን የመለኮት ባሕርይ እንደያዘ መቅረትን አልፈለገም ይልቁንም ያለውን ክብር በገዛ ፈቃዱ ትቶ አገልጋይ መሆን መረጠ በሰው ምሳሌ ተገለጠ እንደ ሰው ሆኖ በትህትና ራሱን ዝቅ አደረገ እስከሞት ድረስ ያውም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ::

## 2. የክርስቶስ ስቅለት

### ሀ. በቁርዓን

እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸውም /ረገምናቸው/ አልገደሉትም አልሰቀሉትምም ግን ለእነርሱ /የተገደለው ሰው በዒሳ/ ተመሰለ:: እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት ከርሱ /መገደል/በመጠራጠር ውስጥ ናቸው ጥርጣሬን

ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም በእርግጥ አልገደሉትም:: /ሱራ 4፥157/

ይህ የቁርዓን ጥቅስ ኢየሱስ በመስቀል ተሰቅሎ እንዳልሞተ የሚናገር ክፍል ነው የተሰቀለው እርሱ ሳይሆን በእርሱ የተመሰለው ነው ይላሉ:: ይህ ማለት በሙስሊሞችም ዘንድ በጣም የተከበሩ ታላላቅ ነቢያቶችና ዓላህን ሐሰተኛ ማድረግ ነው:: ምክንያቱም ዒሳ እንደሚሰቀል ነቢያቶች ስለተናገሩ ነው::

አላህም ባለ ጊዜ /አስታውስ/ ዒሳ ሆይ! ወሳጂህ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ ከነዚያም ከካዱት ሰዎች አጥርህ ነኝ እነዚያንም የተከተሉህን እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ ከነዚያ ከካዱት በላይ አድራጊ ነኝ ከዚያም መመለሻችሁ ወደ እኔ ነው በርሱ ትለያዩበት በነበራችሁት ነገር በመካከላችሁ እፈርዳለሁ:: ሱራ 3፥55

እነዚያ ለማንኛውም መልእክተኛ እሳት የምትባለው የኸነን ቁርባን እስከሚያመጣልን ድረስ ላናምን አላህ ወደኛ አዟል ያሉ ናቸው ::መልእክተኞች ከኔ በፊት በታምራትና በዚያም ባላችሁት /ቁርባን/ በእርግጥ መጥተውላችኋል እውነተኞች ከኾናችሁ ታዲያ ለምን ገደላችኋቸው በላቸው:: ሱራ 3፥183 ይህ የቁርዓን ክፍል በትክክል ስለ ክርስቶስ ተሰቅሎ መሞት ይናገራል:: ምክንያቱም በታምራትና በድንቆች ወደ አይሁድ መጥቶ የተገደለ ከኢየሱስ በቀር ማንም የለም:: ዓላህ የሚወደውን ነቢይ እንድሰቀል አሳልፎ አይሰጥም ብለው ይላሉ ይህ ክፍል ግን ነቢያት አልፈው መሰጠታቸውና መሞታቸው ይናገራል::

ሙሳንም መጽሐፍን በእርግጥ ሰጠነው ከበኋላውም መልክተኞችን አስከታተልን የመርየም ልጅ ዒሳንም ግልጽ ታምራቶችን ሰጠነው በቅዱስ መንፈስም አበረታነው ነፍሶቻችሁ ለማትወደው ነገር መልክተኛ በመጣላችሁ ቁጥር /ከመከተል/

ትኩራላችሁን? ከፊሉንም ትገድላላችሁ:: ሱራ 2፥87 ዒሳ /ኢየሱስ/ ግልጽ ተአምራቶች እያደረገ በመካከላቸው እየተመላለሰ ሳለ እንደተጋደለ የሚናገር ክፍል ነው::ይህ ከወንጌል እውነት ጋር የሚስማማ ሀሳብ ነው አይሁዳውያን ኢየሱስን (ዒሳ) ከአላህ ዘንድ ተልኮ ወደ እነርሱ በመጣ ጊዜ አልተቀበሉትም እንዲያውም በቁርዓን እንዳነበብነው አልተባበሩትም ተቃውመውታል ገድለውታል::

ለ. በመጽሐፍ ቅዱስ

ከዚሁ ሀሳብ ጋር የሚስማማ ከአዲስ ኪዳን (ከኢንጅል) በዝርዝር እንመለከታለን ጳውሎስ ከእናንተ ጋር በነበርኩበት ጊዜ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር በተለይም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ከመሞቱ ጉዳይ ሌላ ምንም ነገረ ላለማወቅ ወስኜ ነበር ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች እንዲህ አላቸው ከእናንተ የእግዚአብሔርን ምስጥር አስተማርኳችሁ እንጂ የንግግር ችሎታና የፍልስፍና ጥበብን አይደለም የጳውሎስ ትምህርት የሚያተኩረው ክርስቶስ ለሰው ልጅ ኃጢአት መሞቱ ከሞት መነሳቱን ነው:: ማወቅ የሚፈልገውም ሆነ የሚያስተምረው የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤውን ነው::

ኃጢአት ወደ ሞት የሚያስገባ በር ነው:: ከአብያተ ክርስቲያናት እንደ ተማርነው ትምህርት ኃጢአት መንፈሳዊ በሽታ ነው:: ኃጢአት የእግዜአብሔር ትዕዛዝ መተላለፍ ነው:: "ነገር ግን ደጉን ከክፉ ለመለየት የሚያስችል እውቀት ከሚሰጠው ዛፍ ፍሬ አትብላ ምክንያቱም ከዚህ ዛፍ ፍሬ በበላህበት ቀን በእርግጥ ትሞታለህ" ብሎ አዘዘው:: ዘፍ. 2፥17 ኃጢአት የሚሰራ ሰው ራሱ ይሞታል ሕዝ. 18፥4

ምክንያቱም ሰዎች ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል:: እግዚብሔር የሰጣቸውን ክብር አጥተዋል ሮሜ. 3፥23:: የሰው ዘር የተባለ ሁሉ በየትኛውም የሃይማኖት ጥላ ሥር ያለ ከኃጢአት የሚያድን አዳኝ

ያስፈልገዋል:: አይሁድም ሆኑ አሕዛብ ሁሉም ከኃጢአት በታች ናቸው:: እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል:: "አንድ እንኳ ፃድቅ ሰው የለም አስተዋይም የለም ሁሉም ከእውነት መንገድ ወጥተው ተሳስተዋል ደግ ሥራ የሚሰራ አንድ ሰው እንኳ የለም ሮሜ 3፥9-12"

ከጳውሎስ በፊት ኢሳያስ እንዲህ ብሎ ተንብዮአል:: እኛ እያንዳንዳችን ከመንገድ ወጥተን በመባዘን እንደ ጠፋ በጐች የሆነን ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር እኛ ልንቀበለው የሚገባንን ቅጣት ሁሉ በእርሱ ላይ አኖረ:: ኢሳ. 53፥6

እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ነው ፅድቁ ትክክለኛ ፍርድ አምጥቶአል:: እግዚአብሔር ፈራጅ ብቻ አይደለም ፍቅር ጅምር እንጂ:: ይህ ሲባል በፍርዱ ኃጢያትን ከቀጣ የተትረፈረፈው ፍቅሩና ምህረቱ ደግሞ ድነንነት ያመጣል እርሱ በፍርዱና በፍቅሩ ትክክል ነው ካልን ሁለት ነገሮች እንድንቀበል እንገዳዳለን ፍርዱ ቅጣትን ያመጣል ፍቅሩና ምህረቱ ከሞት ያድናል::

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንድኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአል:: ዩሐ 3፥16 መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ደህንነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው ሰውን ማዳን የሚችል እርሱ ብቻ ነው:: ምህረትና እውነት ተገናኙ ጽድቅና ሰላም ተስማሙ መዝ 85፥10

ወደ ቀይ ባህር በሚወስደው መንገድ በመጓዝ ሳሉ ትግስታቸው አለቀ በእግዚአብሔርና በሙሴ ተነስተው በምድረ በዳ እንድንሞት ከግብፅ ያወጣችሁን ለምንድን ነው? ምግብ የለ ውሃ የለ ይህን የማይረባ ምግብ ሰውነታችን ተጸይፎታል ሲሉ ተናገሩ:: በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር መርዘኛ እባብ ላከባቸው:: ሕዝቡን ነደፉ ብዙ እስራኤላውያንም ሞቱ ሕዝቡ ወደ ሙሴ መጥተው በእግዚአብሔርና

በአንተ ላይ በመናገራችን በድለናል እባቦች ከእኛ እንዲያርቅልን ወደ እግዚአብሔር ፀልይልን አሉ ሙሴም ስለ ሕዝቡ ፀለየ:: በእግዚአብሔር ትዕዛዝ የነሃስ እባብ ሰርቶ ሰቀለ በእባብ የተነደፈ ማናቸውም ወደናሱ እባብ በተመለከቱ ጊዜ ይድኑ ነበር::ዘኁ. 21፥5-9

"ጌታ እንዲህ አለ ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ልስቀል ይገባዋል:: ዩሐ. 3፥15

እስቀላለሁ ብሎ የተናገረው ራሱ ነው:: የአላህ ሩህ የሆነውን ዒሳ ሳይሰቀል እሰቀላለሁ ብሎ አይናገርም ሰው ሰውን የሚዋሽው ብዙ ጊዜ ከፍርሀት የተነሳ ነው :: ኢየሱስ (ዒሳ) ግን ማንንም አይፈራም:: የሰማኸው ቃል እንግዳ ቢሆንብህና ባይገባህ ቶሎ ብለህ እውነት አይደለም በሚል ልብህን አትዝጋ። ከዚህ በፊት ስለ ክርስቶስ ስቅለት ትክክል ባልሆነ መንገድ ሰምተህ ከሆነ እውነትን ለማወቅ ጊዜው አሁን ነው የመዳን ቀን ዛሬ ነው::

እስራኤላውያን በአላህ ላይ በማመፃቸው ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ሰጣቸው ከደረሰባቸው መከራና ጭቆና አንድ የተደጋገመ ፀሎት ይፀልዩ ነበር። የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ ተነስ ተነስ ኀይልን ልበስ እያሉ በቀድሞ ዘመናት የሰራቸውን ተዓምራቶች አባቶቻቸውን ከፈርኦን እጅ ማዳኑ የቀይ ባህር በተአምራት መከፈል በማስታወስ ይፀልይዩ ነበር:: እግዚአብሔር ፀሎታቸውን ሰምቶ ዒሳን ላከላቸው ያለማመናቸውን የተረዳው ነቢይ እንዲህ አለ የሰማነውን ነገር ማን አመነ የእግዚአብሔር ክንድ ለማን ተገለጠ?

በእርግጥ እርሱ ደዌያችንን ወሰደ ህመማችንም ተሸከመ እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደተመታ እንደተቀሰፈ ቆጠርነው:: ነገር ግን እርሱ ስለመተላለፋችን ተወጋ ስለበደላችንም ደቀቀ በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት በእኛ በደል አልፎ የተሰጠውን ዒሳ በመስቀል ላይ

በሚስማር ተቸንክሯል ደሙን ስለእኛ አፍስሶአል ይህ ደም ነው የኃጢአት ይቅርታ ያስገኘልን።

እርሱ በግፍ ተይዞ ተፈረደበት ወደ ሚገድሉበትም ቦታ ተወሰደ ወገን እንደ ሌለው ተቆጠረ ስለ ሕዝባችን ኃጢያት ሞት ተፈረደበት ከሕያዋን ምድር ተወገደ። ኢየሱስ /ዒሳ/ በመስቀል ላይ የሰራው ሥራ ለማወቅ አስፈላጊውን ነገር ፈቃድህን ለእግዚአብሔር ሰጥተህ የበለጠ ለመማር መዘጋጀት ነው።

ሐዋሪያው ጴጥሮስ ጌታ ስለ ሚገጥመው መከራ በሚናገርበት ጊዜ በዚህች ሌሊት ሁላችሁም ትክዱኛላችሁ ባለ ጊዜ ጴጥሮስ ሁሉም ቢክዱህ እኔ አልክድህም አለ። በቂጣ በዓል መጀመሪያ ቀን ደቀመዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው የፋሲካን ራት የት እንድናዘጋጅልህ ትፈልጋለህ አሉት? እርሱም በከተማ ወደ ሚኖረው ወደ እንትና ቤት ሂዱና መምህር ጊዜየ ቀርቦአልና ከደቀመዛመርቴ ጋር የፋሲካን ራት የምበላው በአንተ ቤት ነው ይላል በሉት። ሲበሉም ኢየሱስ በእውነት እላችኋለሁ ከእናንተ አንዱ እኔን አሳልፎ ይሰጣል አለ። የሰው ልጅ ስለ እርሱ በተፃፈው መሰረት ይሞታል ነገር ግን የሰውን ልጅን አሳልፎ የሚሰጠው ወዮውለት ያ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር። አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳ መምህር ሆይ እኔ እሆንን? አለ ኢየሱስም አንተ እንዳልከው ነው አለው። በተፃፈው መሰረት ያለው ጌታ ኢየሱስ /ዒሳ/ የብሉይ ኪዳን ነቢያቶች ስለ ሰው ልጅ ኃጢአት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንደሚሞት ተንብየው ነበር ያንን ለማመልከት ነው።

በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን እንዲህ አላቸው እረኛ ውን መትቼ እገድላለሁ የመንጋውንም በጎች ይበተናሉ ተብሎ ተጽፎአልና በዚህች ሌሊት ሁላችሁም ትክዱኛላችሁ ነገር ግን ከሞት ከተነሣሁ በኋላ ወደ ገሊላ ቀድሜአችሁ እሄዳለሁ። በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ሌሎቹ ሁሉ እንኳን ቢክዱህ እኔ ከቶ አልክድህም ብሎ

ተናገረ ኢየሱስም በእውነት እላለሁ ዛሬ በዚህች ሌሊት ዶሮ ከመጮኹ በፊት አንተ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ አለው:: ጴጥሮስ ግን መሞት እንኳን የሚያስፈልግ ቢሆን ከአንተ ጋር እሞታለሁ እንጂ ከቶ አልክድህም አለው::

ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከደቀመዛመርቱ ጋር ጌቴ ሴማኒ ወደ ሚባል ስፍራ ሄደ:: እዚያም እንደ ደረሱ ኢየሱስ ደቀመዛርቱን እኔ እዚያ ሄጄ እስከጸልይ እናንተ እዚህ ቆዩ አላቸው::

ከፀለየ በኋላ ወደ ሦስት ደቀመዛሙርት ተመልሶ በመጣ ጊዜ ተኝተው አገኛቸው:: ስለዚህ ጴጥሮስን እንዲህ አለው ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት እንኳን መንቃት አልቻላችሁምን? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ፀልዩ የሰው መንፈስ ሁል ጊዜ ዝግጁ ነው ሥጋ ግን ደካማ ነው::

እንደገናም ኢየሱስ ለሁለተኛ ጊዜ ርቆ ሄደና አባቴ ሆይ ይህን የመከራ ጽዋ ሳልጠጣው ሊያልፍ የማይችል ከሆነ እንደ አንተ ፈቃድ ይሁን ሲል ጸለየ:: ከዚህ በኋላ ወደ ደቀመዛሙርቱ ተመልሶ መጣና እንዲህ አላቸው አሁንም ገና ተኝታችኋልን? አሁንም ዕረፍት ታደርጋላችሁን እነሆ ሰዓቱ ደርሶአል:: የሰው ልጅ በኃጢያተኞች እጅ ተላልፎ ይሰጣል ተነሱ እንሂድ እነሆ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቦአል::

ኢየሱስ ገና ሲናገር ሳለ እነሆ ከአስራ ሁለቱ አንዱ የሆነው ይሁዳ መጣ ከእርሱ ጋር ሰይፍና ዱላ የያዙ ብዙ ሰዎች መጡ ... ይሁዳም ወዲያውኑ መጥቶ ወደ ኢየሱስ ቀረበና መምህር ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን ብሎ ሳመው ኢሱስም /ጊሰም/ ወዳጄ እንግዲህ የመጣህበትን ጉዳይ ፈፅም አለው::

ጴጥሮስም ከቤት ውጪ በሊቀ ካህናቱ ግቢ ውስጥ ተቀምጦ ነበር በዚያን ጊዜ አንዲት ገረድ ወደ እርሱ ቀርባ አንተም እኮ ከገሊላዊው ኢየሱስ ጋር ነበርህ አለችው:: እርሱ ግን የምትይውን

አላውቅም ሲል በሁሉም ፊት ካደ ሲወጣ ወደ በሩ ሲሄድ አንዲት ሌላ ገረድ እዚያ ለነበሩት ሰዎች ይህ ሰው ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር ነበር አለች ጴጥሮስም ይህን የምትይውን ሰው አላውቀውም በመማል እንደገና ካደ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እዚያ ቆመው የነበሩት ሰዎች ወደ ጴጥሮስ ጠጋ ብለው አነጋገርህ ያስታውቃልና በእርግጥ አንተም ከእነርሱ ወገን ነህ አሉት:: በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ እኔ ይህን ሰው አላውቀውም እያለ ራሱን መራገምና መማል ጀመረ ወዲያውኑም ዶሮ ጮኸ::

ጴጥሮስም ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ብሎ ኢየሱስ የተናገረውን ቃል ትዝ አለው ወደውጪም ወጣና ምርር ብሎ አለቀሰ:: ማቴ. 26፥17-18፤21፥24-25፤31፥34-36፤40-41፤45-47፤69-75

በዚያን ጊዜ የገዢው ወታደሮች ወደ ገዥው ግቢ ወሰዱት ወታደሮችንም ሁሉ በኢየሱስ ዙሪያ ተሰበሰቡ ልብሱንም ገፈው ቀይ ልብስ አለበሱት የእሾክ አክሊልም ጉንጉነው በራሱ ላይ ደፉበት በቀኝ እጁም መቃ አስያዙት በፊቱም እየተንበረከኩ የአይሁድ ንጉሥ ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን እያሉ ያፌዙበት ነበር::

መቃውንም ከእጁ ወስደው ራስ ራሱን በመቃ ይመቱት ነበር ካፌዙበት በኋላ ቀዩን ልብስ አውልቀው የራሱን ልብስ አለበሱት ሊሰቅሉትም ወሰዱት ከገዥው ግቢ ሲወጡ ሳሉ ስምዖን የተባለውን የቃሬና አገር ሰው አገኙና የኢየሱስን መስቀል እንድሸከም አስገደዱት ከዚህ በኋላ ቀራኒዮን ወይም የራስ ቅል እየተባለ ወደ ሚጠራው ሥፍራ ወደ ጉልጉታ ደረሱ በዚያም ከሐሞት ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ለኢየሱስ አቀረቡለት እርሱ ግን ቀመስ አድርጐ ሊጠጣው አልፈለገም:: ከሰቀሉት በኋላ ልብሱን ዕጣ ተጣጥለው ተካፈሉ።

ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ኢየሱስ «ኤሎሄ ኤሎሄ ለማስበቅታኒ» ሲል በታላቅ ድምፅ ጮኸ ትሩጓሜውም አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ ማለት ነው ። ኢየሱስ እንደገና በታላቅ ድምፅ ጮኸና ሞተ።

በመሸም ጊዜ የአርማትያስ ሰው የሆነ ዮሴፍ የሚባል አንድ ሀብታም ሰው ወደዚያ ወጣ እርሱም የኢየሱስ ደቀመዝሙር ነበር። ይህ ሰው ወደ ጲላጦስ ሄደና የኢየሱስ አስከሬን ለመነ ጲላጦስም አስከሬኑ እንዲሰጠው አዘዘ። ስለዚህ ዮሴፍ አስከሬኑን አውርዶ በንፁህ ጨርቅ ከፈነው ከዓለት ተወቅሮ በተዘጋጀው በራሱ አዲስ መቃብር ውስጥ ቀበረው። ከዚህ በኋላ ትልቅ ድንጋይ አንከባሎ የመቃብሩን በር ዘጋና ሄደ። ማቴ. 27፥27-35፣ 46፥50-57-60

ሰንበት ካለፈ በኋላ እሁድ ጠዋት በማለዳ መቅደላዊት ማርያምና ሌላይቱ ማርያም መቃብሩን ለማየት ሄዱ እነሆ በድንገት የምድር መናወጥ ሆነ የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ ወርዶ መቃብሩ የተዘጋበትን ድንጋይ አንከባለለና በላዩ ተቀመጠ የመልአኩም ፊት እንደ መብረቅ ያበራ ነበር። ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ። ከጠባቂዎቹ መልአኩን ከመፍራት የተነሣ በመንቀጥቀጥ እንደ በድን ሆኑ መልአኩ ግን ሴቶቹን እንዲህ አላቸው እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትፈልጉ አውቃለሁ እርሱ ከሞት እነሣለሁ ብሎ እንደተናገረው ተነስቶአልና በዚህ የለም ተኝቶበት የነበረውን ሥፍራ ኑ እና እዩ እንግዲህ በፍጥነት ሄዳችሁ ለደቀመዛሙርቱ ከሞት ተንስቶአል ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል። በዚያን ታገኙታላችሁ ብላችሁ ንገሩአቸው እነሆ እኔ ነግሬአችኋለሁ።

አስራ አንዱ ደቀመዛሙርት ኢየሱስ እንድሄዱ ወደ አመለከታቸው በገሊላ ወደ ሚገኘው ተራራ ሄዱ ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት አንዳንዶቹ ግን ተጠራጠሩ ኢየሱስ ወደ እነርሱ ቀረበና እንዲህ አላቸው ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል እንግዲህ ወደ ዓለም ህዝብ ሁሉ ሂዱ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ

ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀመዝሙርት አድርጓቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንድፈፅሙ አስተምሩአቸው እነሆ እኔ እስከ መጨረሻው ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ማቴ. 28፥1-7፤16-20

ሦስት ጊዜ አላውቀውም ብሎ የካደው ጴጥሮስ በብዙ ሺ ሕዝብ ፊት እንዲህ ብሎ መስክሯል የእስራኤል ሰዎች ሆይ ይህን ቃል ስሙ ራሳችሁ እንደምታውቁት የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተዓምራትና ድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ። እርሱንም በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በዓመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፎቶ አስነሳው ሞት ይይዘው ዘንድ ከቶ አልቻለምና ሐዋ.2፥22-24

ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞትና ከሞት ስለ መነሳቱ ሥመስክር እንዲህ ብሎአል:: እኔ የተቀበልኩትን በመጀመሪያ ደረጃ ያለውን ነገር ለእናንተአስተላለፍ ሁላችሁ ያስተላለፍሁላችሁም ነገር በቅዱሳት መጽሐፍት እንደተፃፈው ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ ተቀበረ በቅዱሳት መጽሐፍት እንደተጻፈው በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሣ የሚል ነው እንዲሁም ለጴጥሮስ ታየ ኋላም ለአስራ ሁለቱ ታየ ከአምስት መቶ ለሚበልጡ ተከታዮቹ በአንድ ጊዜ ታያቸው ከእነርሱ አብዛኛዎቹ እስከ አሁን በሕይወት አሉ:: አንዳንዶቹ ግን ሞተዋል ከዚያም በኋላ ለያቆብ ታየ ለሐዋሪያቶም በሙሉ ታያቸው ::

በመጨረሻም እንደ ጭንጋፍ ለሆንሁት ለእኔ ደግሞ ታየኝ እኔ ከሐዋርያት ሁሉ ያነስሁና ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ ነኝ:: ምክንያቱም እኔ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ያሳደድሁኝ ነኝ:: ነገር ግን አሁን የሆንሁትን የሆንሁት በእግዚአብሔር ፀጋ ነው::የተሰጠኝ ፀጋ ያለ ፍሬ አልቀረም እንዲያውም ከሌሎች ይበልጥ በሥራ ደከሜአለሁ:: ነገር ግን ይህን ያደረገው ከእኔ ጋር ያለው

የእግዚአበሔር ፀጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም:: እንግዲህ እኔም ሆንሁ እነርሱ የምናስተምረው ይህንኑ ነው እናንተም ያመናችሁት ይህንኑ ነው:: 1ቆሮ. 15፥3-11 ጳውሎስ በተደጋጋሚ በቅዱሳት መጽሐፍ እንደተጻፈው የሚለው ስላሳ ዘጠኝ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት መጥቀሱ ነው::

ቁርዓን ለምንድን ነው የተጻፈው? ወደ አንተ መጽሐፉን /ቁርዓንን /ከበፊቱ ያለውን አረጋጋጭ እና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ስኾን በእውነት አውረድን ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ቁርዓን የወረደው ተውራት ዘቡርንና ኢንጂልን ለማረጋገጥ ነው እንጂ ለመቃወም አይደለም ሱራ 5፥48

መሀመድ ካንተ በፊት መልእክተኞች የተባለው እንጂ ለአንተ ሌላ አይባልም ሱራ 41፥43 የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን ትምህርት የሚያፀና መልዕክት እንጂ የሚያፈርስ መልእክት አላወረድንልህም ነው መልእክቱ::

ወደ አንተ ካወረድነው ቁርዓን በመጠራጠር ውስጥ ብትኾን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን ታውራት ዘቡርንና ኢንጅልን የሚያነቡት ጠይቅ ሱራ 10፥94 ሁሉም ባይሆኑም አንዳንድ ሙስሊም ወገኖቻችን ከላይ የተጠቀሰውን የቅዱስ ቁርዓን ጥቅስ የማይታዘዙ አሉ እንኳን የማይገባቸው የመጸሐፉ ሰዎች ጠይቀው ሊረዱ ቀርቶ ስለ ኢንጂል መስማት የማይፈልጉ ብዙ ናቸው ይህን ትዕዛዝ ተግባራዊ አለማድረግ አላህን አለመታዘዝ ነው::

በጳውሎስ ዘመን የስህተት አስተምህሮ ያላቸው ሰዎች ተነስተው ነበር ከሞት በኋላ ሕይወት ወይም ትንሳኤ የለም የሚል ነው አስተምሮአቸው:: ጳውሎስ ለትምህርታቸው በሰጠው መልስ ኢየሱስ እንደ ሞተና ከሞት እንደ ተነሣ እንዲሁ ከሞት በኋላ ትንሳኤ እንዳለ ምሳሌአችን ነው:: ነገር ግን ክርስቶስ ከሞት እንደተነሣ

የምናስተምር ከሆነ ከእናንተ አንዳንዶቹ ከሞት መነሳት የለም እንዴት ይላሉ?

ከሞት መነሣት ከሌለማ ክርስቶስ ከሞት አልተነሣም ማለት ነው? ክርስቶስ ከሞት ካልተነሣ የእኛ ትምህርት ሆነ የእናንተ እምነት ከንቱ መሆኑ ነዋ! ደግሞ እግዚአብሔር ክርስቶስን ከሞት አስነስቶታል ብለን በማስተማራችን ሐሰተኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነናል ማለት ነዋ!

እንግዲህ የሞቱት ሰዎች ከሞት ካልተነሱ እግዚአብሔር ክርስቶስንም ከሞት አላስነሳውም ማለት ነው? ክስርስቶስ ከሞት ያልተነሣ ከሆነ እምነታችሁ ከንቱ ነዋ! ገና በኃጢአታችሁ እንደሞታችሁ ናችሁ ማለት ነዋ! በክርስቶስ አምነው በሞት ያንቀላፉትም ጠፍተዋል ማለት ነዋ! ክርስቶስ ተስፋ ያደረግነው ለዚህ ዓለም ህይወት ብቻ ከሆነ ከሰዎች ሁሉ ይልቅ የሚታዘንልን መሆናችን ነዋ! ነገር ግን ክርስቶስ ለሞቱት ከሞት የመነሣት የመጀመሪያ ምሳሌ ሆኖ በእርግጥ ከሞት ተነስቶአል:: ሞት የመጣው በአንዱ ሰው በአዳም ምክንያት እንደሆነ ከሞት መነሣትም የሚመጣው በአንዱ ሰው በክርስቶስ ምክንያት ነው:: በአዳም ምክንያት ሰው ሁሉ እንደሚሞት እንዲሁ በክርስቶስ ምክንያት ሰው ሁሉ ህይወትን ያገኛል::

በኢንጂል እንደተፃፈው ወንጌል ሰውን የማዳን ሀይል አለው::እኔ በወንጌል አላፍርም ምክንያቱም የወንጌል ቃል በመጀመሪያ ለአይሁዳውያን ቀጥሎም ለአረማውያን የሚያምኑትን ሰዎች ሁሉ ማዳን የሚችል የእግዚአብሔር ኀይል ነው:: ይህም የወንጌል ቃል እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያጸድቀው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው በእምነት ሕይወትን ያገኛል ተብሎ ተጽፎአል:: ሮሜ 1፥16-17

## ፈቃደኛ ከሆንክ ይህን ፀሎት ፀልይ

እባህ አንተ መሃሪ ቸር አምላክ ነህ ዒሳ ለእኔ የሰራውን ሥራ አላምንም ነበር፡፡ ቅዱስ ቁርዓናችን የመጽሐፉ ሰዎች ትክክለኞች እንደሆኑና እነርሱ የሚሉንን መስማትና መቀበል እንዳለብን አዞናል፡፡ እነርሱም ዒሳ ስለ እኛ ኃጢአት ሞቶአል እኛንም ወክሎ ከሞት ተነስቶአል ይላሉ፡፡ እባክህ ፈጣሪዬ ይህን ምስጢር ግለጥልኝ በኢንጂል እንደተፃፈው የዘላለም ሕይወት እንዳገኝ ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ ልጅህ አድርገህ ተቀበለኝ፡፡ አሜን ፡፡

### 3. በቁርዓን ለኢየሱስ የተሰጠው ስያሜ

የመሪየም ልጅ ዒሳ አልመሲሕ /ኢየሱስ/ በቁርዓን ከተገለፁት ነቢያትም ሆነ የፈጣሪ መልዕክተኛ ተብለው ሥያሜን ከተሰጣቸው የፈጣሪ አገልጋዮች ዒሳ /አልመሲህ/ የላቀ አገላለፅ ልዩ የክብር ስያሜ ከስሙም ጋር የተያያዘ የተለየ ባህርይ አለው፡፡ በኢየሱስ መልእክተኛ ነት የማያምን ማንም እርሱ እስላም አይደለም፡፡

ቁርዓን ሥጋ ለባሽ ያልገባበት በሰው ችሎታና ድርጊት ያልተገለጡ በኢየሱስ ብቻ ተገልጠው የታዩ ልዩ ልዩ አስገራሚ ድርጊቶችን ይተርካል እያንዳንዱ የስሙ መግለጫና ካገለገለው አገልግሎትና ከማንነቱ ጋር በጥብጥቅ ይያዛል፡፡ በቁርዓን አልመሲሕን /ኢየሱስ ክርስቶስን/ በአስራ አምስት ምዕራፎች ከዘጠና ሦስት ጊዜ በላይ ተጠቅሷል፡፡ ይህ የሚያመለክተው በቁርዓን ለጌታ ከፍ ያለ ቦታ እንዳለው ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ ሌሎች ታላላቅ ነቢያቶች ያልተሰጣቸው ስም ለኢየሱስ /ዒሳ/ ተሰጥቶታል፡፡ ከተሰጡት ስሞች ሁሉንም ባይሆን የተወሰኑትን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

1. **አልመሲህ** :- የተቀባ ማለት ሲሆን ከአስራ አንድ ጊዜ በላይ ተጠቅሷል፡፡

እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ በሀይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ በአላህ ላይ እውነትን

እንጂ አትናገሩ የመርያም ልጅ አልመሲህ ዒሳ ... ቃሉም ከርሱ የሆነ መንፈስ ብቻ ነው

ሱራ 4፥171 ፤ 3:45 ፤ 5:15 ፤9:30

ይህ አገላለፅ መጽሐፍ ቅዱስ ከሰጠው ስያሜ ጋር ይስማማል በብሉይ ኪዳን መሲሁ በሚል ሥያሜ ተሰፋ ሆኖ የተሰጠው በአዲስ ኪዳን እውን የምስራች ሆኖ ወደ ዓለም መምጣቱን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: በፈጣሪ ተቀብቶ ወደእኛ መምጣቱ ምን ማለት ይሆን? የዚህ ምስጥር እንድገለጥሎዎት አላህን በፀሎት ይጠይቁ::

እግዚአብሔር ሆይ ማየት እንድችል ዓይኖቹ ከፈትለት ብሎ ፀለየ እግዚአብሔርም ፀሎቱን ሰምቶ አይኖቹን ከፈተለት:: 2ነገ. 6፥17

2. አብድአላህ:-የአላህ /የእግዚአብሔር/ ባሪያ ማለት ነው:: ቁርዓን ይህን መጠሪያ ለኢየሱስ ሰጥቶታል::

ሕፃኑ አለ እኔ የአላህ ባሪያ መጽሐፍ ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጎኛል ሱራ 19፥30 ሕፃኑ ይህንን ንግግር የተናገረው ገና በአንቀልባ ሳለ ነው:: የአይሁድ የመረጃ መጽሐፍትም ይህን ያስተጋባሉ:: ገና በአንቀልባ ሳለ የነበረው ህፃን የባርነትን ስፍራ መርጦ ለፈጣሪ ልባዊ መገዛትን ለማሳየት መፍቀዱን እንዴት እንገነዘበዋለን ?

ብሉይና ሐዲስም የባርያን መልክ ሊይዝ የፈቀደውን አዳኝ ሁሉን ትቶ መምቱን ይነግሩናል ጻድቅ ባሪያዬ የባሪያን መልክ ይዞ ሊያገለግልና ነፍሱን ... የሚለው አገላለፅ ከዚህ እውነት ጋር አንድ መስመር ላይ ሆኖ ይታያል:: በፍቃዱ ራሱን ለባርነት መስጠቱን ምን መልእክት አለው?

3. አንካብ፡- የቃሉ ትርጉም ነብይ ማለት ነው። ቁርዓን እንዲህ ይላል ሕፃኑ እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ መጽሐፍም ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጎኛል። ሱራ 19፡30 ከፈጣሪ የተላከ ነቢይ እንደሆነ ያስገነዝበናል። መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው የተላከ አስገራሚና ስልጣን ያለው መምህር መሆኑን በተራራው ስብከት ሲያበሥር፣ደብረዘይት ተራራ የተናገረው ትንቢት እንዲሁም አጠቃላይ የምድር ኑሮው፣ነብይ ብሎ ራሱን መጥራቱን በህዝብ መጠራቱ የተናገረው በሙሉ እንዳለው መፈፀሙ የነቢይ አገልግሎት እንደነበረው በተጨባጭ ያስረዳል። ስለዚህ ክርስቲና ከዚህ አገላለፅ ጋርም አይጋጭም። ችግሩ ነቢይ የሚለው ብቻውን መጉላቱ ነው። ነቢይ ብቻ እንዳይደለ በተራ ቁጥር አራት ይመልከቱ ።

4. ከልመት አላህ /ካለማተሁ/ ፡- የስሙ ትርጉም የአላህ /የእግዚአብሔር/ ቃል ማለት ነው። በቁርዓን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል ለመሆኑ የእግዚአብሔር ቃል ከማንነቱ የተለየነውን? ይህ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው። ያ በእርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው። ሱራ 19፡34

ቃሉም ከርሱ የሆነ መንፈስ ብቻ ነው። ሱራ 4፡171 እነዚህ የቁርዓን ጥቅሶች ዒሳን የእግዚአብሔር ቃል መሆኑ አስረግጠው ነግረውናል።መጽሐፍቅዱስም ኢየሱስን የእግዚአብሔር ቃል ብሎ ጠርቶታል። በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም ከእግዚአብሔርም ጋር ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ እርሱ በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል ከተፈጠረውም ሁሉ ያለ እርሱ የተፈጠረ ምንም የለም። ዮሐ. 1፡1-3

እግዚአብሔር ዓለምንና በዓለም ያለውን ሁሉ የፈጠረ ሕያው ቃል ሆኖ መላኩ በቁርዓን ከተገለጠው ይህ የእግዚአብሔር ቃል ምን

ያህል ልብ ይባል ይሆን ቁርዓን ኢየሱስን የእግዚአብሔር ቃል ሲል ምን ማለቱ ነው::

5. ሩሁሚንሁ:- የስሙ ትርጉም የእርሱ የሆነ መንፈስ ማለት ነው:: ከኢየሱስ ሌላ ይህ ስም ለሌላ ለማንም አልተሰጠም ለመሆኑ መልዕክተኛው የተባለው ነው ወይስ መንፈስ ነው ለፈጣሪ የሚቀርበው? ታዲያ መንፈስ ተብሎ ከተጠራው ይልቅ መልእክተኛ ተብሎ የተጠራው እንዴት ተመረጠ የመርያም ልጅ አልመሲህ ዒሳ ... ቃሉም ከርሱ የሆነ መንፈስ ብቻ ነው:: ሱራ 4፥171 መንፈስ ተብሎ መጠራቱ ምን ማለት ይሆን?

6. አያት አላህ:- የቃሉም ትርጉም የፈጣሪ ምልክት ወይም ታምር ማለት ነው :: ያችንም ብልቷን የጠበቀችውን በርሷም ውስጥ ከመንፈሳችን የነፋንባትን እርሷንም ልጇን /እንደዚሁ ለዓለም ተዓምር ያደረግናትን/ መርያምን አስታውስ ሱራ 21፥19
   የመሪየም ልጅና እናቱ ታምር አደረግናቸው የመደላደልና የምንጭ ባለቤት ወደሆነች ከፍተኛ ሥፍራ አስጠጋናቸው ሱራ 23፥50

   ፈጣሪ ለትውልድ ሁሉ ማሳየት የፈለገው አስደናቅው ነገር በዚህ ምልክት ውስጥ ተቀምጧል አስተዋይ ብቻ ነው ይህን ምክር ገንዘቡ የሚያደርገው::ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለህፃናት ስለገጥህላቸው አመስግንሀለሁ አዎን አባት ሆይ ፈቃድህ በፊትህ እንዲህ ሆኖአልና:: ማቴ. 11፥25

7. ማታል አላህ:- ይህ እንደ እብራይስጡ ማሻል ማለት ነው:: የስሙ ትርጉም ምሳሌ ማለት ነው:: የመርየም ልጅ ምሳሌ በተደረገ ሕዝቦችህ በእርሱ ይስቃሉ ሱራ 43፥5

መድሐፍ ቅዱስ በብዙ ሥፍራ የእርሱ ምሳሌነት በሰው ልጆች በተለይም በአማኞች ሕይወት ያለው ሥፍራ ከኑሮአችን ጋር የተያያዘ ነው።

ይህ እውነተኛ ምሳሌ ኢየሱስ እንከን የሌለው ይሰማው ዘንድ ለወደደ ሰው ሁሉ ድንቅ ምክር አለው የእርሱ የመጀመሪያው ምክር ልባችሁ አይጨነቅ በእግዚአብሔር እመኑ በእኔም ደግሞ እመኑ ... ኢየሱስም እንዲህ አለው መንገድ እኔ ነኝ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ዩሐ.1፥41-6

ክፉ አድርጋችሁ ቅጣት ስትቀበሉ ብትታገሱ ምን ምስጋና ይኖራችኋል? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራ ስትቀበሉ ብትታገሱ ከእግዚአብሔር ምስጋና ታገኛላችሁ። የተጠራችሁትም ለዚህ ነው። ምክያቱም የእርሱን አርአያነት እንድትከተሉ ክርስቶስ መከራን በመቀበል ምሳሌ ሆኖላችኋል። 1ጴጥ. 2፥20-21

8. ራሱል አላህ የሚለው ቃል ትርጉሙ የተላከ ማለት ነው።

ጽሕፈትንና ጥበብንም ተውራትንም ኢንጂልንም ያስተምረዋል። ወደ እስራኤል ልጆች መልእክተኛ ያደርገዋል ሱራ 3፥48-49

መጽሐፍ ቅዱስም መልክተኛው ለሰው ልጆች ሁሉ የሚጠቅም የከበረ እውነት ይዞ መምጣቱንና በበደላቸውና በኃጢያታቸው ሞተው በሞት ክልል የሚርመሰመሱትን ወደ ህይወት የሚያሻግር እውነተኛው ድልድይ ኢየሱስ ነው።

እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌ የሚሰማ በላከኝ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም። ዩሐ. 5፥24

9. ሸሒድ፡- የቃሉ ትርጉም ምስክር ማለት ነው። በእውነት እርሱ እውነተኛ መስካሪ ነው በትንሳኤ ቀን መስካሪ ነው።በትንሳኤ ቀን መስካሪ ሆኖ እንደ ሚቆም ቁርዓን ይናገራል።ከመጽሐፉም ሰዎች

ከመሞቱ በፊት በእርሱ በዒሳ በእርግጥ የማያምን አንዲም የለም በትንሳኤ ቀን በእርሱ ላይ መስካሪ ይሆናል:: ሱራ 4፥159
ከላይ የሚመጣ ከሁሉም በላይ ነው:: ከምድር የሆነ ምድራዊ ነው የምድርን ነገር ይናገራል ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው:: እርሱ ያየውንና የሰማውን ይመሰክራል ነገር ግን የእርሱን ምስክርነት የሚቀበል የለም:: የእርሱን ምስክርነት የሚቀበል ግን እግዚአብሔር እውነተኛ መሆኑን ያረጋግጣል::
ዮሐ. 3፥31-33

10. ዋጂሁ:- የስሙ ትርጉም የተከበረ ማለት ነው::እንዲህ የተባለለት ነቢይም ሆነ መልክተኛ የለም ከአላህ ልዩ መልክተኛ ከአልመሲህ በስተቀር መላዕክት ያሉትን አስታውስ መርየም ሆይ አላህ ከእርሱ በሆነው ስሙ አልመሲህ ዒሳ የመርየም ልጅ ያበስርሻል ሱራ 3፥45::
መጽሐፍ ቅዱስ ዒሳ የከበረና ከፍ ያለ መሆኑን ሥገልፅ በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ወዳለው የክብር ሥፍራ ከፍ አደረገው ከስም ሁሉ የሚበልጠውን ስም ሰጠው:: ስለዚህ ለኢየሱስ ስም ክብር በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በጉልበታቸው ይንበረከካሉ በምላሳቸውም ኢየሱስ ክርስቶስ በእርግጥ ጌታ ነው ብለው በመመስከር ለእግዚአብሔር አብ ክብር ይሰጣሉ:: ፊል. 2፥9-11

11. ረሂማ:- ይህ ማለት ደግሞ ምህረት ማለት ነው::እግዚአብሔር ሌላ ምንን ሊያስገነዝብ ይችላል? በእኔ ላይ ገር ነው:: ቀና አለና ከእናንተ መካከል ኃጢያት የሌለበት በመጀመሪያ ድንጋይ ይወርውርባት አላቸው:: ከዚህ በኋላ እንደገና ጐንበስ ብሎ በመሬት ላይ ፃፈ:: ሱራ 19:26

እነርሱም ይህን በሰሙ ጊዜ ከሽማግሌዎች ጀምሮ ሁሉ አንድ በአንድ ከዚያ ሄዱ ስለዚህ ኢየሱስ ከሴትየዋ ጋር ብቻውን ቀረ:: ከዚህ

በኋላ ኢየሱስ ቀና ብሎ አንቺ ሴት ከሳሾችሽ የት አሉ? የፈረደብሽ ማንም የለም? አላት:: እርሷም ጌታ ሆይ ማንም የለም አለችው :: ኢየሱስም እኔም አልፈርድብሽም ሂጅ ዳግመኛ ኃጢያትን አትሥሪ አላት:: ዩሐ. 8፥7-11

በእውነት ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ የቸርነት ስጦታ ነው:: በምህረቱ ወደ እግዚአብሔር ቤት እንገባለን በምህረቱ ባለጠጋ የሆነው እግዚአብሔር ምህረቱ ለዘላለም ስለሆነ ረሂማን ሰጠን::

12. ሚነልሙቀርቢን /የቀረበ/ ወደ ቸሩ ፈጣሪ በጣም የቀረበ፣የተጠጋ ማለት ነው:: ለመሆኑ የትኛው ማመን ይቀላል? አልመሲህ ዒሳ የመርየም ልጅ በዚህ ዓለምና በመጨረሻው ዓለም የተከበረ ከባለሟሎች በሆነ ልጅ ያበስርሻል ሱራ 3፥45-46

እግዚአብሔርን ያየው ማንም የለም ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ያለው አንድ ልጁ ብቻ ገልጦታል ዩሐ. 1፥18

ዒሳ ለእግዚአብሔር የቀረበ ብቻ አይደለም ሰዎችንም ወደ ራሱና ወደ አላህ የሚቀርብ ነው::

በማግስቱ ዩሐንስ ከሁለት ተማሪዎቹ ጋር እንደገና እዚያ ቆሞ ነበር ዩሐንስ ኢየሱስ በዚያ ሲያልፍ አይቶ እነሆ የእግዚአብሔር በግ አለ::

ሁለቱም የዩሐንስ ደቀመዝሙርት ዩሐንስ ይህን ሲል ሰምተው ኢየሱስን ተከተሉት:: ኢየሱስ መለስ ብሎ ሲከተሉት አየና ምን ትፈልጋላችሁ? አላቸው

እነርሱም ረቢ የምትኖረው የት ነው? አሉት / ረቢ ማለት መምህር ማለት ነው::/ እርሱም ኑና እዩ አላቸው ስለዚህ ሄዱና የት እንደሚኖር አዩ:: በዚያን ቀን ከእርሱ ጋር አብረው ዋሉ ጊዜው ወደ አሥር ሰዓት ገደማ ነበር::

ዲሳ ለእግዚአብሔር የቀረበ ብቻ አይደለም ሰዎችንም ወደ ራሱና ወደ አላህ የሚቀርብ ነው:: ዲሳ ለደቀመዛሙርቱ ጓደኛ በመሆን አብሮአቸው ያሳልፍ ነበር:: ከህብረተሰቡ ራሱን በማግለል እኔ ሩህ አላህ ነኝ /የእግዚአብሔር መንፈስ ነኝ/ በማለት ደሆችንና በሽተኞችን አልረሳም በቀንና በሌሊት ሰዎች ወዳሉበት በመሄድ አስተማረ እንጂ::

በማግስቱ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ለመሄድ ፈለገ ፊልጶስም አገኘ ውና ተከተለኝ አለው :: ፊልጶስም እንደ እንድርያስና እንደ ጴጥሮስ የቤተ ሳይዳ ከተማ ሰው ነበረ:: ፊልጶስም ናትናኤልን አግኝቶ ሙሴ በሕግ መጽሐፍ ነቢያትም በትንቢት መጻሕፍት ስለ እርሱ የጻፉለትን አገኘነው እርሱም የዮሴፍ ልጅ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው አለው::

ናትናኤል ግን ከናዝሬት መልካም ነገር ከቶ ሊገኝ ይችላል? አለው ፊልጶስም መጥተህ እይ አለው :: ኢየሱስ ናትናኤል ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እነሆ ተንኮል የሌለበት እውነተኛ የእስራኤል ሰው ሲል ስለ እርሱ ተናገረ:: ናትናኤልም እንዴት አወቅኸኝ አለው::

ኢየሱስም ፊልጶስ ሳይጠራህ በፊት ከበለስ ዛፍ ሥር ሆነህ አይቼሀለሁ ስል መለሰለት:: በዚህ ናትናኤል መምህር ሆይ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ አለ::

ኢየሰሱም እንዲህ አለ አንተ ያመንኸው ከበለስ ዛፍ ሆነህ አይቼሀለሁ ስላልኩህ ነውን? ከዚህ የበለጠ ነገሮች ገና ታያለህ:: እውነት እውነት እላችኋለሁ ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔር መላእክትም በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ:: ዩሐንስ ወንጌል 1፥37-39፣43-51 ዲሳን የሚከተል ሁሉ የዘላለም ሕይወት ያገኛል::

13. አል ሙባረክ :- የስሙ ትርጉም የተባረከ ማለት ነው በየትም ሥፍራ ብሆን ብሩክ አድርጎኛል::

ሱራ 19፥31 የሰው ዘር በሙሉ ማንን መስማት እንዳለበት አላህ ስያመለክት እንዲህ ብሎአል ከደመናውም ውስጥ የመረጥሁት ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ:: ሉቃ. 9፥35

እንግዲህ እርሱን ስሙት ተብለናል ብሩክ ስሆነው ከሰማይ ለመጣልን መልእክተኛ ያለን መታዘዝና እምነት ወደ ተባረከው ኑሮ ያመጣናል :: የተባረከው ተስፋችንም ይመጣል ::

በዚህ ዓይነት የተባረከው ተስፋችንን እንጠብቃለን ይህም የምንጠብቀው ተስፋ የታላቁ አምላካችንና የአዳኛችን የኢየሱስ ክርስቶስ የክብር መገለጥ ነው:: ክርስቶስ ከዐመፃ ሁሉ ሊያድነንና መልካም ሥራ ለመስራት ትጉሆችና ለእርሱ የተለየን ንፁህ ሕዝብ እንድንሆን ያነፃን ዘንድ ስለ እኛ ራሱን አሳልፎ ሰጠ::

ቲቶ. 2፥13-14

እነዚህ ከላይ የተገለጡት ስሞች ከኖረው ኑሮና ከምድራዊ አገልግሎቱ ጋር ይያያዛሉ ዒሳ በምድር ሳለ ብዙ ምሳሌነት ያላቸው እኛን የየእለቱ አካሄዳችንን የሚደግፍ መልካምነቱ በጎነቱ ከህይወቱ ብናይም በክርስትና ከህይወቱ ይልቅ በሞቱ ታሪካችን ከእርሱ ጋር በጥብቅ ይያያዛል::

## *14. ዒሳ*

ዒሳ የሚለው ስም አዘውትረው የሚጠቀሙበት ስም ነው:: ይህ ስያሜ በቁርዓን ሃያ አምስት ጊዜ ተጠቅሷል ዒሳ የሚለው ስም ኤሳው ከሚለው ስም እንደተወሰደ የሚናገሩ አሉ::

1. ሙሳንም መጽሐፍን በእርግጥ ሰጠነው በኋላውም መልክተኞችን አከታትለን የማርያምን ልጅ ዒሳንም ግልጽ ታምራቶችን ሰጠነውም በቅዱስ መንፈስ አበረታነው::
2. በአላህ እናምናለን ... ወደ ሙሳና ኢሳ በወረደው እናምናለን /ሱራ 2፥136/

3. መላእክት ያሉትን አስታውስ ማርያም ሆይ አላህ ከርሱ የኾነው ቃል ስሙ አልመሲህ ዒሳ የማርየም ልጅ
4. ዒሳ ከነርሱ ክሕደት በተሰማውም ጊዜ ወደ አላህ /ተጨምረው/ ረዳቶቼ እነማን ናቸው አለ ሐዋሪያት እኛ የአላህ ረዳቶች ነን በአላህ አመነናል:: እኛም ትክክለኛ ታዛገሮች መኾናችንን መስክር አሉ::ሱራ3፥52
5. አላህ ባለ ጊዜ አስታውስ ዒሳ ሆይ እኔ ወዳጂህ ወደ እኔ አንሺህ ነኝ:: /ሱራ 3፥35/
6. አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አዳም ብጤ ነው::/ሱራ 3፥59/
7. በአላህ አመንን በኛ ላይ በወረደው በቁርዓን ለኢብራሂምና ... ለሙሳ ለዒሳ:
8. እኛ የአላህ መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን /ሱራ 4፥157/
9. እኛ ወደ ... አብርሃም... ዒሳ /ሱራ 4፥163/
10. እናንተ በአላህ ላይ እውነትን እንጅ አትናገሩ የማርያም ልጅ አልመሲህ ዒሳ /ሱራ 4፥171/
11. ከእስራኤል ልጆች እነዚያ የካዱት በዳውድና በመርየም ልጅ ዒሳ ሁሉም ተረገሙ:: ሱራ 5፥78
12. አላህ በሚል ጊዜ አስታውስ የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ በአንተና በእናትህ ላይ የዋልኩላችሁን ፀጋዬን አስታውስ /ሱራ 5፥110/
13. የመርየም ልጅ ዒሳንም ግልጽ ታምራቶችን የሰጠነው በቅዱሱ መንፈስም አበረታ ነው::
14. ሐዋርያትም የመሪየም ልጅ ዒሳ ሆይ ጌታህ በኛ ላይ ከሰማይ ማእድን ሊያወርድልን ይችላል?

15. የመርየም ልጅ ዒሳ አለ ጌታችን አላህ ሆይ ለኛ ለመጀመሪያዎቻችንና ለመጨመረሻዎቻችን ባዕል /መደሰቻ/ የመትኾንን ከአንተም ተአምር የኾነችን ማእድ ከሰማይ በኛ ላይ አውርድ ስጠንም አንተ ከሰጪዎች ሁሉ በላጭ ነህና:: ሱራ 5፥114

16. አላህም የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ አንተ ለሰዎች እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሀልን:: ሱራ 5፥116

17. ዘከሪያንም የሕያንም ዒሳንም ኤልያስንም /መራን/ ሁሉም ከመልካሞቹ ናቸው:: /ሱራ 6፥85/

18. ይህ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው ::/ሱራ 19፥34/

19. ከነብዮችም የጠበቀ ኪዳናቸውን ከአንተም ከኑሕም ከኢብራሂምም ከሙሳም ከመርየም ልጅ ዒሳም በያዝን ጊዜ /አስታውስ/ ከነርሱም የከበደ ቃል ኪዳን ያዝን:: ሱራ 33፥7

20. ለናንተ ከሃይማኖት ያንን በርሱ ኑሕን ያዘዘበትን ደነገገላችሁ ያንንም ወዳንተ ያወረድነውን ያንንም በርሱ ኢብራሂምን ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን ሃይማኖት በትክክል አቋቁሙ /ሱራ 42፥13/

21. ዒሳ በታምራቶች በመጣ ጊዜም አላቸው በእርግጥ በጥበብ መጣኋችሁ የዚያንም በርሱ የምትለያዩበትን ከፊሉን ለእናንተ ላብራራላችሁ /መጣሁ/ ፍሩ ታዘዙኝም:: /ሱራ 43፥63/

22. ከዚያም በድካምዎቻቸው ላይ መልክተኞቻችንን አስከታተልን የመርየም ልጅ ዒሳንም አስከተልን ኢንጂልንም ሰጠነው በነዚያም በተከተሉት /ሰዎች/ ልቦች ውስጥ መለዘብን

እዝነትን አዲስ የፈጠሩዋትንም ምንኩሰና አደረግን / ሱራ 57፥27/

23. የመርየም ልጅ ዒሳም የእስራኤል ልጆች ሆይ /ሱራ 61፥6/

24. እናንተ ያመናችሁ ሆይ የመርየም ልጅ ዒሳ ለሐዋርያቶቹ ወደ አላህ ረዳቴ ማን ነው?/ሱራ 61፥14/

እስካሁን የተመለከትነው ዒሳ የሚለው ቃል በቁርዓን ምን ያህል ጊዜ እንደተፃፈ አይተናል:: ኢየሱስ በቁርዓን የአላህ/የእግዚአብሔር/ ቃል ተብሎአል:: ቃል የሚለው በቁርዓን ብዙ ቦታ ተጠቅሷል:: ለአሁኑ ሁለት ምዕራፎችን ለማጣቀሻ እንመለከታለን::

ሀ. መላእክት ያሉትን /አስታውስ/:- መርየም ሆይ አላህ ከርሱ በኾነው ቃል ስሙ

አልመሲሕ ዒሳ /ሱራ 3፥45/

ለ. አልመሲሕ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ ወደ መርየም የመጣላት / የኾነ/ ቃሉም ከርሱ

የኾነ መንፈስም ብቻ ነው::/ሱራ 4፥171/

ከነዚህ ሁለት ጥቅሶች ክርስቶስ የተሰጠው ስም ቃል ወይም ከእርሱ የሆነ ቃል የሚል ነው:: በቁርዓን ቃል የሚለው ለዒሳ /ለኢየሱስ/ ብቻ የተሰጠ ነው:: በቁርዓን ለሌላ ለማንም ይህ ስም አልተሰጠም:: ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር ይስማማል::

## 4. የኢየሱስ መለኮትነት በቁርዓን

የኢየሱስን መለኮትነት አስመልክቶ የሚነሳው ክርክር በእስላሞች ብቻ የተወሰነ አይደለም አንዳንድ የሃይማኖት ድርጅቶች ኢየሱስ አምላክ አይደለም ሲሉ ሌሎች ደግሞ የለም እንዲያውም እርሱ ብቻውን አምላክ ነው አብ መንፈስ ቅዱስ የሚባል ነገር የለም

የሚሉ የሀይማኖት ድርጅቶች አሉ ያም ሆነ ይህ ቁርዓን ግን የኢየሱስ መለኮትነቱ የሚገልፁ የሰራቸው ተዓምራቶችን ይተርካል::

1. ካለማት አላህ: የእግዚአብሄር ቃል ማለት ነው:: ያ በእርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው ሱራ 19፥34 በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ እርሱም በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ::ዮሐ. 1፥1-2
2. ሩህ አላህ ወይም የእግዚአብሔር መንፈስ ብሎ ጠርቶታል::ሱራ 4፥171 እግዚአብሔርንና መንፈሱን

   ለያይቶ ማየት አይቻልም::
3. ዒሳ (ኢየሱስ) ታላላቅ ተአምራቶችን ሰርቶአል ቁርዓን ከኢየሱስ ሌላ ማንንም በታምር ሰሪነት አያነሳም ለኢየሱስ ብቻ ይህ ስም መስጠቱ አምላክ የመሆኑን ማስረጃ ልሆን ይችላል::
4. ማሪጉ ቁርዓን ከኢየሱስ ሌላ ሰው አረገ አይልም:: ሱራ 4፥158
5. ፈጣሪ መሆኑ የሕይወት እስትንፋስ መስጠቱ ለአምላክ ብቻ የተሰጠ ችሎታ ሆኖ ሳለ

ቁርዓን ኢየሱስ ፈጣሪ እንደሆነ ይናገራል:: ሱራ 3:49 ፤ 5:110-115

6. በሕፃኑነቱ /በጨቅላነቱ/ መናገሩ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ በእናቱ እቅፍ ያለ ሕፃን

እንደተናገረ አልተሰማም:: ኢየሱስ ብቻ ነው ለምን ሱራ? 19፥29-30

<u>*5. ጌታ ኢየሱስ ለምንድን ነው ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ዓለም የመጣው?*</u>

ሀ. እግዚአብሔርን ለእኛ እንደሚገባን አድርጐ ለመግለፅ ከቶውንም እግዚአብሔርን ያየ ማንም የለም ነገር ግን በአብ እቅፍ ያለው አንድያ ልጁ የሆነው አምላክ እርሱ ገለጠው ዩሐ 1፥18 ከሀያው ቃል የተወሰደ::

ለ. ለኑሮአችን ምሳሌነትን ሊተውልን 1ጴጥ. 2፥21 የተጠራችሁትም ለዚህ ነው ምክንያቱም ክርስቶስ ስለ እናንተ መከራን የተቀበለው የእርሱን ፈለግ እንድትከተሉ ምሳሌን ሊተውላችሁ ነው።

ሐ. ለሰው ኃጢአት መስዋዕት ለመሆን ዕብ. 10፥1

የሙሴ ሕግ ወደ ፊት ለሚመጣው መልካም ነገር ምሳሌ ነበር እንጂ እውነተኛ መልክ አልነበረውም ፣ስለዚህ በየዓመቱ ዘወትር የሚሰውትን መሥዋዕቶች ይዘው ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ሰዎች ፍጹማን ሊያደርጋቸው ከቶ አይችልም።ሕግ ፍጹማን ሊያደርጋቸው ቢችልማ ኖሮ እነርሱ መስዋዕትን ማቅረብ በተዉ ነበር።ምክንያቱም ለአምልኮ የሚቀርቡት ሰዎች በማያዳግም ሁኔታ ከኃጢአት ስለ ነፁ ኃጢአት እንደ ሌለባቸው በኅሊናቸው ይታወቃቸዋል። እነዚህ መስዋዕቶች ግን በየዓመቱ ኃጢያትን የሚያስተሰናባቸው ናቸው። ምክንያቱም የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢየአትን ለማስወገድ አይችልም።

ስለዚህ ክርስቶስ ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ እንዲህ አለ መሥዋዕትንና መባን አልፈለግህም ሰውነትን ግን አዘጋጀህልኝ በሚቃጠል መሥዋዕትና ስለ ኃጠአት ስርየት በሚሰዋ መስዋዕት አልተደሰትህም በዚያን ጊዜ እምላኬ ሆይ በመጽሐፍ ስለ እኔ እንደተፃፈው ፈቃድህን ለመፈፀም መጥቻለሁ አልሁ።

በመጀመሪያ እነዚያን በሕጉ መሰረት የሚቀርቡትን መሥዋዕትንና መባን የሚቃጠለውን መሥዋዕት አልፈለግህም በእነርሱም አልተደሰትህም። ጌታም አለ እነሆ ፈቃድህን ለመፈፀም መጥቻለሁ። በዚህ ሁኔታ ሁለተኛውን ዓይነት መስዋዕት በቦታው ለመተካት የመጀመሪያው ዓይነት መሥዋዕት ተሽሮአል።

በዚህም ፈቃድ በሚለው ቃል መሰረት ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ በማያዳግም ሁኔታ መሥዋዕት ሆኖ በመቅረቡ ምክንያት ተቀድሰናል::

መ. የዲያብሎስን /ጂኒ/ ሥራ ለማፍረስ

ኃጢአት የሚያደርግ ከድያብሎስ ነው:: ምክንያቱም ዲያብሎስ ከመጀመሪያ አንስቶ ኃጢአት የሚያደርግ ነው:: የእግዚአብሔር ልጅ የተገለጠው የዲያብሎስን ሥራ ያፈረስ ዘንድ ነው:: 1ዮሐ.3፥8

ሠ. ሊራራልን የሚችል ሊቀካህን እንዲሆን ::

የዕብራውያን 4፥14-16 እንግዲህ ወደ ሰማያት ያረገ ታላቅ ሊቀካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን እምነታችን አጥብቀን እንያዝ :: በድካማችን የማይራራልን ሊቀካህናት የለንምና ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን ይሁን እንጂ ምንም ኃጢያት አልሰራም:: እንግዲህ ምህረትን እንድንቀበልና በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ፀጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ ::

ረ. ጻድቅ ፈራጅ እውነተኛ ብቁ ዳኛ ሊሆንልን:: ዩሐ. 5፥22-27

አብ በማንም ላይ አይፈርድም ነገር ግን የፍርድን ሥልጣን ሁሉ ለወልድ ሰጥቶአል:: ይንንም ያደረገው ሰዎች ሁሉ አብን እንድያከብሩ እንዲሁም ወልድን እንድያከብሩ ነው:: ወልድን የማያከብር ወልድን የላከውን አብንም አያከብርም:: እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማና በላከኝም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው:: እርሱ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ አይፈረድበትም :: እውነት እውነት እላችኋለሁ:: የሞቱ ሰዎች የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል

ጊዜውም አሁን ነው:: የሚሰሙትም ሁሉ በሕይወት ይኖራሉ:: ምክንያቱም አብ ራሱ የሕይወት ምንጭ እንደሆነ እንዲሁ ወልድን የህይወት ምንጭ እንዲሆን አድርጕታል:: የሰው ልጅ በመሆኑ ፍርድ እንድፈርድ ሥልጣን ሰጥቶታል::

## IV. ለሙስሊሞች እንዴት ነው መመስከር ያለብን ?

ወደ እነርሱ በመሄድ እንደ ደረስን በቁጣ ወይም በስድብ መጀመር የለብንም የበረከት ቃል በመናገር እንጀምር ሙስሊሞች የበረከት ቃል የሚናገራቸውን ሰው እንደ ነቢይ ስለሚቆጥሩት ከአላህ ዘንድ የተላከ ነው በማለት ይቀበሉታል:: ለመመስከር ወጥተን ያገኘነው ሰው ገበሬ ከሆነ አላህ የዘራኸውን ዘር ይባርክልህ ጕተራው ሙሉ ይሁን የዘራኸውን ዘር ይጠብቅልህ ከብቶችህ ከመብዛታቸው የተነሣ በረት ይጥበባቸው እንበለው ነጋዴ ከሆነ በንግድ ሥራው እንዲሳካለት እንባርከው ::

ክፉውን በክፉ ወይም ስድብን በስድብ ፈንታ አትመልሱ በዚህ ፈንታ ባርኩ ምክንያቱም እናንተ የተጠራችሁት እንደ እነዚህ ያሉትን ነገሮች እያደረጋችሁ በረከትን ለመውረስ ነው:: በምናውቀው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ተነስተን ብንፈርድባቸው መገንዘብ ያለብን ሙስሊም ወንድሞቻችን ከጥንት ጀምሮ ከአባቶቻቸው የሰሙት መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል የመጀመሪያ ይዘቱን ሳይሆን ያለው አሁን በሰው ሀሳብ ተተክቶአል ብለው ነው የሚያምኑት መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ ትልቅ መረጃችን ነው በእነርሱ ዘንድ ግን ተቀባይነት የለውም::

አቅጣጫ ለውጠን ለእነርሱ በጥናትና በታሪክ እውነት እና በመረጃ በመታገዝ ወንጌልን እንስበክ ብንል ይህ መንገድ ፍርያማ አያደርገንም:: ለዚህም ሁለት ምክንያቶች አሉ:: የመጀመሪያው ሙስሊም ወገኖቻችን ሃይማኖታቸው በውይይት እና በምክንያት

የተመሰረተ አይደለም። ታላቁ እና የተፈራው አላህ እንዲህ ብሎአል። ሰላም ለነቢያችን ይሁን እሳቸው እንዲህ እና እንዲያ ብለዋል ኢማም እገሌ እንዲህ ብለዋል በሚል የተመሰረተ ነው ። ከላይ በጠቀስናቸው መንገዶች ለመስራት ብንሞክር ስኬታማ አንሆንም።

ሁለተኛው ሐይማኖታዊ ውይይት በምክንያት እና በታሪካዊ እውነት አስመርኩዘን ብንከራከር የፀጋን አገልግሎት ያስወግዳል ወደ ደረቅ ሀይማኖታዊ ክርክር ይለወጣል እንዲህ ዓይነቱ ውይይት ወደ አገር ወይም ወደ ዓለም አቀፍ ፖለቲካ ከተለወጠ የተነሣንበት ዓለማ ይሰናከላል። "ነገር ግን ጠብ እንዳያመጣ አውቀህ፣ ከሰነፎችና ካልተማሩ ምርመራ ራቅ የጌታም ባሪያ ለሰው ሁሉ ገር ለማስተማርም የሚበቃ በትግስትም የሚፀና ሊሆን እንጂ ሊጣላ አይገባውም"። 2 ጢሞ. 2፥23-24

ታዲያ ምንድን ነው ማድረግ ያለብን ምንም ነገር የመግቢያ ቃል ሳንጠቀም አንተ ስማ ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንተ ሞቶልሃል። ጌታን ብትቀበል ይሻልሃል ያለዚያ ትጠፋለህ ወደ ሲኦል ትገባለህ። ይህን የሰማው ሙስሊም ወንድምህ የአእምሮ ችግር አለበት ብሎ ዘወር ይላል ወይም የሰማው ነገር ሳይገባው እንግዳ ነገር ሰምቶ ይሄዳል። የወንጌል ሰባኪው ለመጀመሪያ ጊዜ ወጣቱን ሙስሊም አግኝቶ አንተ አለው ዘወር ሲልለት ደካማ ሃጢያተኛ ነህ ቢሆንም አትፍራ የጌታ የኢየሱስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃል ብሎ ሳይጨርስ ወዲያው ይህ ወጣት ተበሳጭቶ ከዚያ አካባቢ ጠፋ።

ወንድሜ የተሰማራኸው በእግዚአብሔር እርሻ ነው።ሙስሊሞችን ወደ ጌታ ለማምጣት ቃላት መምረጥ አለብህ ለጆሮአቸው እንግዳ የሆነ ከዚህ በፊት ሰምተውት የማያውቁት ቃላት አትጠቀም ቀላል የሆነ ለመረዳት የማያስቸግር ለእነርሱ የሚሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተጠቀም።

*ለምሳሌ አብርሃም፦* የእምነት አባት የሆነው አብርሃም የይሳሀቅ አባት እንደሆነ ሁሉ የእስማኤልም አባት ነው። በዚህ ዘመን በክርስትና እና በእስልምና መሀል ገብቶ የሚያቀራርብ ማን ነው ቢባል አብርሃም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አብርሃም እንዲህ ይላል። አብርሃም ርስት አድርጐ ወደ ሚቀበለው ሥፍራ እንዲሄድ በተጠራ ጊዜ በእምነት ታዘዘ ወዴት እንደሚሄድ ባያውቅም እሺ ብሎ ሄደ። በባእድ አገር እንዳለ መጻተኛ በተስፋይቱ ምድር በእምነት ተቀመጠ የተስፋውም ቃል አብረውት እንደሚወርሱት እንደ ይሳቅና እንደ ያዕቆብ በድንኳን ኖረ ምክንያቱም መሠረት ያላትን እግዚአብሔር የሠራትና፣የፈጠራትን ከተማ ይጠባበቅ ነበር አብርሃም ምንም እንኳን እድሜው ቢገፋም ሣራም ራሷ መካን ብትሆንም ተስፋ የሰጠው ታማኝ አድርጐ ስለቆጠረ በእምነት የልጅ አባት ለመሆን በቃ ስለዚህ እንደ ሞተ ሰው ከሚቆጠር ከዚህ ከአንድ ሰው እንደ ሰማይ ከዋክብት የበዛና እንደ ባህር ዳር አሸዋ ተቆጥሮ የማያልቅ ዘር ተገኘ። ዕብ. 11፥8-12

አብርሃም በቁርዓን የተናገረውን ቃል ከአብራሃም ምዕራፍ የሚከተውን አብረን እናንብብ። ኢብራሂም ባለ ጊዜ አስታውስ ጌታዬ ሆይ ይህንን አገር መካን ጸጥተኛ አድርገው እኔንም ልጆቼንም ለጣዖታት ከመገዛት አርቀን ጌታ ሆይ እነርሱ /ጣዖታት/ ከሰዎች ብዙዎችን አሳስተዋልና የተከተለኝም ሰው እርሱ ከኔ ነው ትዕዛዜንም የጣሰ ሰው አንተ መሐሪ አዛኝ ነህ ጌታችን ሆይ እኔ አዝመራ በሌለው ሸለቆ ውስጥ በተከበረው ቤት /በከዕባ/ አጠገብ ከዘሮቼ አስቀምጥሁ ጌታችን ሆይ ሶላትን ያቋቁሙ ዘንድ/ አስቀመጥኳቸው/ ከሰዎችም ልቦችን ወደነሱ የሚናፍቁ አድርግ ያመሰግኑህም ዘንድ ከፍሪዎች ስጣቸው ጌታችን ሆይ! አንተ የምንደብቀውንም የምንገልጸውንም ሁሉ በእርግጥ ታውቃለህ በአላህም ላይ በምድርም በሰማይም ምንም ነገር አይደበቅም።

ለዚያ ከሽምግልና በኋላ ኢስማዒልን ኢስሐቅንም ለኔ ለሰጠኝ አላህ ምስጋና ይግባው ጌታዬ ልመናን በእርግጥ ሰሚ ነውና፣ ጌታዬ ሆይ ሶላትን አዘውትሬ የምሰግድ አድርገኝ ከዘሮቼም /አድርግ/ ጌታችን ሆይ ለእኔም ለወላጆቼም ለምእመናንም ሁሉ ምርመራ በሚደረግበት ቀን ማር:: አላህንም በደለኞች ከሚሰሩት ግፍ ዘንጊ አድርገህ አታስብ የሚያቆያቸው ዓይኖች በርሱ እስከሚፈጡበት ቀን ድረስ ብቻ ነው::/ወደ ጠሪው መልእክ/ ቸኳዮች ራሶቻቸውን አንጋጮች ኾነው/ዓይኖቻቸው ይፈጣሉ/ ዓይኖቻቸው ወደ እነርሱ አይመለሱም ልቦቻቸውም ባዶዎች ናቸው:: ሰዎችንም ቅጣቱ የሚመጣባቸው ወደ እነርሱ አይመለሱም ልቦቻቸውም በዶዎች ናቸው:: ሰዎች ቅጣቱ የሚመጣባቸውን ቀን፣አስፈራራቸው እነዚያም የበደሉት ጌታችን ሆይ ወደ ቅርብ ጊዜ ድረስ አቆየን ጥሪን እንቀበላለንና መልክተኞቹንም በማለት የማላችሁ አልነበራችሁም?/ ይባላሉ/::

በእነዚያም ነፍሶቻውን በበደሉት ሰዎች መኖሪያ ውስጥ ተቀመጣችሁ በነርሱም እንዴት እንደሰራንባቸው ለእናንተ ተገለጸላችሁ ለናንተም ምሳሌዎችን ገለጽንላችሁ::/በነብዩ ላይ/ ሴራቸውንም በእርግጥ አሴሩ ሴራቸውም /ቅጣቱ/ አላህ ዘንድ ነው ሴራቸውም ኮረብታዎች /ሕግጋቶች/ በርሱ የሚወገዱበት አልነበረም:: አላህንም መልእክተኞችን የገባላቸውን ቃል ኪዳኑን አፍራሽ አድርገህ አታስብ አላህ አሸናፊ የመበቀል ባለቤት ነው:: ሱራ 14፥35-47

ስለ ራሱ ቤተሰብ ስለ መካ ወደ አላህ ማልዷል ይላሉ የፀለየው ከመካ ሁከትን አስወግድ እኔ እና ልጆቼን ጣወታት ከማምለክ አውጣን ኢብራሂም ጣዖትን ከማምለክ ተለይቶ የወጣው እንዲህ ነው:: እግዚአብሔር አብርሀምን እንዲህ አለው አገርህን ትተህ ከዘመዶችህና ከአባትህ ቤተሰብ ተለይተህ እኔ ወደ ማሳይህ አገር ሂድ ዘርህን አበዛዋለሁ ታላቅ ህዝብም ይሆናል እባርክሃለሁ ስምህንም ገናና አደርገዋለሁ ለሌሎችም በረከት ትሆናለህ የሚመርቁህን እመርቃለሁ

የሚረግሙህን እረግማለሁ በአንተ አማካይነት ሕዝቦች ሁሉ ይባረካሉ ::

አብርሃም እግዘአብሔር እንደነገረው ከካራን ወጥቶ ሄደ በዚያም ጊዜ ዕድሜው ሰባ አምስት ዓመት ነበር ሎጥም አብሮት ሄደ::ዘፍ.12፥1-4 እኛ አብርሃም አባታችን ነው እንደምንለው ሁሉ ለእነርሱም አባታቸው ነው::በምንመሰክርበት ጊዜ በአብርሃም ታሪክ ብንጀምር ያደምጡናል:: ቁርዓንን ጨርሶ ሌሎች ትምህርቶች እየተከታተለ ካለ ወጣት ጋር ስለ ሃይማኖት አንስተን ስንወያይ ኢብራሂም በክርስቲያኖች አብርሃም መሆኑ ስነግረው በጣም ገረመው ስለ አብርሃም የህይወት ታሪክ ነገርኩት ዝም ብሎ በደስታ አደመጠኝ:: በሌላ ቀን ስንገናኝ ተመሳሳይ ውይይት እንድናደርግ ጠየቀኝ:: በቡሊይ ኪዳን አባቶች የሕይወት ታሪክ አንስተን በሚንወያይበት ጊዜ ለወደፊት ግንኙነታችን ድልድይ ፈጠርን ማለት ነው ::

ይህም አብርሃም በእግዚአብሄሔር አመነ እምነቱም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት ተብሎ እንደተፃፈው ነው:: እንግዲህ የሚያምኑ ሁሉ የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ እወቁ እግዚአብሔር አረማውያንን በእምነት እንደሚያፀድቅ መጽሐፍ አስቀድሞ አይቶ ህዝቦች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ በማለት አስቀድሞ ለአብርሃም የምስራቹን ቃል አብሥሮአል:: ስለዚህ የሚያምኑ ሁሉ ከአመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ:: ገላ. 3፥6-9

ከላይ ያነበብነው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በምሳሌ ብንጠቀም የበለጠ ሊብራራልን ይችላል:: ኢያሱ ወንጌልን ለሌሎች ለመናገር ሽክም አለው ወደ አለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም አስተምሩ የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በጆሮው አዘውትሮ ያቃጭልበታል:: የሰባኪዎች የመልእክት ርእስ በዚሁ አቅጣጫ ቢሆን ደስ ይለዋል:: በጌታ ፊት ጊዜ ወስዶ ከፀለየ በኋላ ለምስክርነት ወጣ የጌታን ትዕዛዝ

ለመፈፀም በመብቃቱ ደስ እያለው ተራመደ ከፊት ለፊቱ አንድ የተቀመጠ ሰው አየ ወደ ሰውየው ቀረብ ብሎ እንደ ምን ዋልክ ለመጨበጥ እጁን በመዘርጋት ኢያሱ እባላሁ አለው:: የተቀመጠው በተራው ኢብራሂም እባላለሁ በማለት መለሰለት በእናንተ ኢብራሂም ስሆን በእኛ ደግሞ አብርሃም ነው:: የእናንተን አላውቅም በእኛ ታላቅ ነቢይ ናቸው እስልምና የእርሳቸው ሀይማኖት ነው አለ ኢብራሂም ::

ኢያሱ በተከፈተው በር ኢብራሂምን በማስፈቀድ ስለ አብርሃም ታሪክ ነገረው እየሰማ ባለው ታሪክ በጣም ስለ ተመሰጠ የሚቀጥለው ታሪክ ለመስማት በትኩረት ይመለከተዋል::ኢያሱም በመቀጠል አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅ ሆኖም ተቆጠረለት የሚያምን ሁሉ የአብርሃም ልጅ ነው አለው:: ኢብራሂም አልገባኝም እንዴት? አለው እየህ ህዝቦች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ በማለት አስቀድሞ የምሥራቹ ቃል ለአብርሃም አብሥሮለታል:: ስለዚህ የሚያምኑ ሁሉ ካመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ:: ኢብራሂም የምሥራቹ ቃል ያልከው አልገባኝም ምንድን ነው ብሎ ጠየቀው ::

እሱማ እንዴት መሰለህ በህግ በእንጨት ተሰቅሎ የሚሞት ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአል ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከእግርማን ዋጀን ይህም የሆነው እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን በረከት በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ለህዝብ ሁሉ እንዲደርስ ነው ሰዎች ክርስቶስን በማመን የዘላለምን ሕይወት እንድያገኙ ነው አለው::

ኢብራሂም ፈገግ ብሎ እስከ አሁን ያልከው ሁሉ ገብቶኛል:: በመጨረሻ የተናገረኸው ነገር አልገባኝም አሁን ጊዜ የለኝም በሌላ ቀን እዚሁ መገናኘት እንችላለን ብሎት ጨብጦት ተለያዩ::

ለአገልግሎት ማለት ለምስክርነት የሚወጣው ሰው የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ሊኖረው ያስፈልጋል::

## ሀ. በእነርሱ መሀል ስታገለግል

ሀ. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግለሰብ ሆነ ሐይማኖት የሚያንቋሽሽ ቃል አትጠቅም።

ለ. በውይይት ጊዜ አድምጠው በትግስትና በክርስቶስ ርህራሄ ተመልከተው ይህን ካደረግህ

ማስተላለፍ ለምትፈልገው መልእክት ጥሩ ሁኔታ ፈጥረሀል ማለት ነው።

ሐ. ለእነርሱ ወንጌል ለመስበክ ባህላቸውን ማወቅ አለብህ። ይህን የማያደርግ ሰው የተዘጋጀን

ምግብ ሰዎች በሌሉበት ለሰማይ አሞራዎች አቅርቦ ዘወር እንደ ማለት ነው።

መ. ከሁሉም በላይ እነርሱን መውደድ በንፅህና መመላለስ ታማኝነትና መልካም ባህርይ ማሳየት፣ አብረሃቸው በምትሆንበት ጊዜ ለምትናገረው ቃል ጥንቃቄ ማድረግ። የአካባቢውን ሁኔታ በማየት እንዴት ይሆናል ብሎ አለመጨነቅ በመንፈስ ቅዱስ በመታመን ሥራውን መጀመር መንፈስ ቅዱስ ምሪትን ይሰጣል አዝመራውን እንዴት መሰብሰብ እንዳለብህ ያሳውቅሀል።

አንድ ጊዜ አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ሲናገር ሰማሁ ሰላማዊ ክርክር ብናደርግ ስለ እነርሱ ሃይማኖት አመጣጥ በግልፅ ብንነግራቸው የተሻለ ነው ብሎ ተናገረ። ይህ አካሄድ እንደ እኔ መረዳት ጥሩ አይደለም ክርክር አካሔድን ያበላሻል መደናገርን ያመጣል መለያየት እና ጠላትነትን ይፈጥራል ውጤቱ ለወንጌል ልባቸውን ይዘጋሉ። የለዘበች መልስ ቁጣን ትመልሳለች ሸካራ ቃል ግን ቁጣን ታነሣሣለች ምሳ. 15፥1 የእኛ አገልግሎት ቁጣን የሚመልስ መሆን አለበት ቁጣን ማነሳሳት የመንፈሳዊ ሰው ተግባር አይደለም።

አንድ ወጣት አገልጋይ ለሚቃወሙትና ለሚያሳደዱት የሚከተለውን ደብዳቤ ጽፎአል:: አንተ ለእኔ መልካም ሰው አይደለህም ቢሆንም ክርስቶስ እንድወድህ አስተምሮኛል አንተ አትወደኝም በሀይለኛ ጥላቻ ተሞልተህ እየተከታተልህ ትቃወመኛለህ በወንጌል አምነህ የእግዚብሔር ልጅ እንድትሆን ስለ አንተ ዘወትር እፀልያለሁ በእውነት እኔ በጣም ደስተኛ ነኝ እግዚአብሔር አምላክ ትዕዛዙን እንዳደርግ ችሎታ ሰጥቶኛል እኔ አንተን እወድሀለሁ በቤቱ እስካይህ ድረስ እፀልይልሀለሁ::

እነርሱም ወጥተው በየሥፍራው ሁሉ ሰበኩ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሰራ ነበር በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያፀና ነበር ማር. 16፥20 በእኛ ሕይወት የሌለ በሐዋርያት ሕይወት የነበረ እንቅስቃሴአቸው ሁሉ በድርጊት የተሞላ ነበር ቃሉን ያጠናሉ ይፀልያሉ ወጥተው ይመሰክራሉ:: በሴሚናርና በውይይት ሳንወሰን እንውጣ የእነርሱን ፋና ተከትለን ተልእኮአችንን እንፈጽም::

"ከመጀመሪያ ስለነበር ስለ ህይወት ቃል እንጽፍላችኋለን ይህ የሕይወት ቃል የሰማነውና በዓይኖቻችን ያየነው የተመለከትነውና በእጆቻችን የዳሰስነው ነው:: ይህ ሕይወት ተገልጧል እኛም አይተነዋል እንመሰክራለንም:: በአብ ዘንድ የነበረውና ለእኛም የተገለጠውን የዘላለም ሕይወት እንነግራችኋለን::ከእኛ ጋር ሕብረት እንዲኖራችሁ ያየነውንና የሰማነው ለእናንተም እንነግራችኋለን :: ኅብረታችንም ከአብና ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው:: ደስታችን ሙሉ እንድሆን ይህን እንጽፍላችኋለን":: 1ዮሐ. 1፥1-4

ሐዋሪያው ዮሐንስ ወንጌል በቀላል መንገድ ለሌሎች ሲያስተላልፍ ከእኛ ጋር ህብረት እንዲኖራችሁ ብሎ ያነሳቸውን ነጥቦች ልብ ብለን እንመልከታቸው በዓይን አይተነዋል ያለው ጌታ ለሦስት ዓመት ተኩል ከደቀመዛሙርቱ ጋር አብሮ አሳልፎአል::

ከሌሎች ደቀመዛሙርት የበለጠ ይቀርበዋል ጌታ የሚወደው ደቀመዛሙር የሚል ስም አግኝቶአል ለዚህ ነው በዓይን አይተነዋል ያለው ሰዎች እውነትን ለማወቅ ሲፈልጉ ማን ነው? በዓይን ያየው ብለው ይጠይቃሉ ያየው ግለሰብ ሲነግራቸው እሺ ንገረን እውነቱን ማወቅ እንፈልጋለን ቢለው ይላሉ:: እኛ አይተነዋል የሕይወት ቃል ተገልጦአል:: ሰባ የጌታ ተከታዮችና የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ አይቶታል:: በከፍታ በኮረብታማው ጐልጐታ የተሰቀለው ዒሳ ከግንባሩ ከእጁ እና ከእግሩ የሚፈሰውን ደም አይተዋል ወገኖቹና አብረውት የኖሩት በመስቀል ተሰቅሎመሞቱና በሦስተኛው ቀን መነሳቱን መስክረዋል::

በማየት ብቻ አልተወሰነም ሰምተነዋል ይላል ሐዋሪያው:: በተራራ፣ በባህር፣ በጀልባ ላይ ሆኖ በምድረ በዳ ሲያስተምር ሰምተውታል የሰው ልጅ የሚሰማው ነገር ያድነዋል ወይም ያጠፋዋል:: የሕይወት ቃል መስማት ግን ከሞት ያስመልጣል ሰዎች ቃል ሰምተው ይቀርባሉ ቃል ሰምተው ይርቃሉ:: አዳም ከሙታን ዓለም የሞትን ቃል ሰማ ከሰማው ቃል የተነሣ ከኤደን ገነት ለመውጣት እግሮቹን አንስቶ ተራመደ::በዚህ ዘመን የሰይጣን ድምፅ የሰሙ እግሮቻቸው ከሕያዋን ጉባኤ የራቁ በጣም ብዙ ሰዎች ናቸው:: በእግዚአብሔር ሥራ እና በመንፈስ ቅዱስ ሐሴት ያደርጉ የነበሩ እንግዳ የሆነው ድምፅ ሰምተው የሰሙትን ቃል ጠራርጐ ወስዷቸዋል::

ለ. <u>አገልግሎትህ በፍቅር የተቀመመ መሆን አለበት</u>::

ለሙስሊሞች ወንጌልን ለመስበክ ትልቁ መሳሪያ ፍቅር ነው:: በዚህ ምክንያት የሚከተሉት ነገሮች እንዲጨመሩላችሁ ትጉ:: በእምነት ላይ ደግነትን በደግነት ላይ ዕውቀትን በዕውቀት ላይ ራስ መግዛትን በራስ መግዛት ላይ በትግስት መጽናትን በትዕግስት በመጽናት ላይ መንፈሳዊነት ላይ ወንድማማችነትን በወድማማችነት

ፍቅርን ጨምሩ:: እነዚህ የመንፈሳዊ ዓለም ቁልፍ በሕይወታችን በብዛት ቢኖሩ ሰዎች ጌታን ወደ ማወቅ እናመጣቸዋለን የወንጌል አገልግሎታችን በጅምር አይቀርም::

አንዳንድ ሰዎች ክርስትና እና እስልምና ልዩነት የላቸውም ተመሳሳይ ናቸው ይላሉ:: በእርግጥ ይህ አባባላቸው ያቀራርበናል ጥሩ ነገር ነው::ሁለቱም የአንድ አምላክ አስተምህሮ ነው ያላቸው በዚያው ልክ ልዩነቶችም አሉ:: የእስልምና የሐይማኖት መሪዎች በኢንጂል/ወንጌል/ እናምናለን ይላሉ:: ለሕዝባቸው ግን ወንጌልን አያስተምሩም ወንጌል ዒሳ አዳኝና ጌታ ነው የሚል ነው:: ይህ እውነት በሙስሊሞች ዘንድ ተዘንግቶአል ሞትና ትንሳኤውም ጭምር::

ቅዱሳት መጽሐፍት እንደሚያስረዱት አይሁዶች ሀይማኖተኞች ናቸው በአንዱ በእግዚአብሔር ያምናሉ:: እግዚብሔር ከመካከላቸው ሐዋሪያቶች አስነስቶ መዳን በክርስቶስ መሆኑን ከእርሱ ውጭ ደህንነት እንደሌለ መስክረው አልፈዋል ተራው የእኛ ነው::ሰውን ከእግዚአብሔር የሚያስታርቅ አገልግሎት ተሰጥቶናል::

ይህም እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት ሰዎችን ሁሉ ከራሱ ጋር አስታረቀ ማለት ነው:: በደላቸውንም አልቆጠረባቸውም ለእኛ የማስታረቅ ቃል ሰጠን:: እግዚአብሔር ሰዎችን በእኛ አማካይነት ስለሚጠራ እኛ በክርስቶስ ስም አምባሳደሮች ነን:: ስለዚህ ከእግዚአሔር ጋር ታረቁ ብለን በክርስቶስ ስም እንለምናችኋለን:: እኛ ከክርስቶስ ጋር በመተባበር የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን እግዚአብሔር ኃጢአት የሌለበት ክርስቶስ የእኛን ኃጢያት እንዲሸከም አደረገው 2ቆሮ. 5፥19-21 ሁለተኛው የጳውሎስ ደብዳቤ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክት እንዲህ ይላል "እኛ ራሳችንን አንሰብክም ነገር ግን ክርስቶስ ጌታ የሆነውን እንሰብካለን የጠራን ለዚህ ነው"::

ይህ እንዳለ ሆኖ የሰባኪው ባህርይ ምን ዓይነት መሆን አለበት "መልካሙን ሥራችሁን ዓይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ" ማቴ. 5፥16

የጨለማ ቁራጭ በህይወታቸው የታየ ሰዎች ተስተካከሉ ሲባሉ መልሳቸው ልቤን እግዚአብሔር ስለሚያውቀው ለሚወራው ወሬ ግድ የለኝም ይላሉ:: ይህ ክርስቶስ የሰጠን ብርሃን ማጨለም ነው:: ብርሃናችን መብራት ያለበት አብረውን ባሉ ሰዎች ፊት ነው:: ብርሃን ሲባል በቤታችን ያለው የኤሌክትሪክ አንፑል ብቻ ከታየን የመልእክቱን ሀሳብ አላገኘነውም:: ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ ማለት ከሰዎች ጋር አብረን በምንኖርበት ጊዜ መልካም ሥራ መስራት እርስ በእርስ መዋደድ በውጭና በቤት ምሳሌነት ያለው ኑሮ መኖር በኛ ቤት የበራው ብርሃን በጐረቤታችን እንዲበራ ወንጌል መናገር ማለት ነው::

እኔ ከክርስቶስ ጋር እንደተሰቀልሁ ያህል ስለምቆጥር ከእንግዲህ ወዲህ ክርስቶስ በእኔ ይኖራል:: እንጂ እኔ ለራሴ ሕይወት የምኖር አይደለሁም አሁንም በሥጋ የሚኖርበት ሕይወት በወደደኝ እና ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ በማመን በተገኘው ሕይወት ነው:: ገላ. 2፥20

አንድ ተቀጣሪ ሰራተኛ ከአለቃው ጋር የዘወትር ግንኙነት እንዳለው ሁሉ አገልጋይም ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበና የማያቋርጥ ህብረት ሊኖረው የግድ ነው::ጌታን የሕይወት ምሳሌ አድርጐ መከተል ቃሉን በማጥናትና በፀሎት የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ ማለዳ ተነስቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳ ሂዶ በዚያ ፀለየ ማር. 1፥35

የእኛ ትልቁ ስህተት ከመውጣታችን በፊት እንዴት ይቻላል በማለት መወሰናችን ነው:: ብዙ ክርስቲያኖች ሙስልሞች የደህንነት

ወንጌል አይቀበሉም ብለው ያምናሉ ስእነርሱ መስበክ ትክክል አይደለም ጊዜን ማባከን ነው ይላሉ:: እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ያለው ሰው ወጥቶ እንዴት ፍሬያማ ልሆን ይችላል:: በዘመናችን ወንጌልን ሰምተው የዳኑ ብዙ ሙስሊሞች አሉ::ከእነርሱ መሀል አንዱ እኔ ነኝ:: ይልቅ ፍቅርን ለብሰን የሕይወት ቃል ይዘን ወደ እነርሱ መራመድ ከእኛ ይጠበቃል::

ከአፌ የሚወጣው ቃል በከንቱ ወደ እኔ አይመለስም ነገር ግን የምሻውን ያከናውናል የተላከበትንም ዓላማ ይፈፅማል ኢሳ. 55፥11 የመዳንን ወንጌል መስበክና የጌታ ደስታ ከእነርሱ ጋር መካፈል አለብን:: በፀጋው ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ እናመጣለን አንዲት ነፍስ ብትሆን በጌታ ዘንድ የከበረች ናት ወደ ጌታ ከመጡት ሰዎች በአንጼ ቅፅበታዊ ለውጥ አለመጠበቅ ከነስህተታቸው መቀበልና መውደድ:: ማስታወስ ያለብን አንድ ነገር አለ ይኸውም እኛ ወደ ቤቱ እንደመጣን ቅፅበታዊ ለውጥ አላሳየንም ተሳስተው ስናያቸው በአባትነት መንፈስ ከስህተታቸው መመለስ እንደጓደኛቸው እስኪቆጥሩን አብረናቸው ማሳለፍ ይህንን ካደረግን አገልግሎታችን ፍሬያማ ያደርገዋል::

ወንድሞች ሆይ ሰው በማናቸውም በደልስንኳ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየዋህነት መንፈስ አቅኑት አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ ገላ. 6፥1 ትልቅ ችግር የሆነው መንፈሳዊ ሰው መጥፋቱ ነው::

ስህተትን በማለፍ በመምከር በማሰተማርና በትእግስት በመጠባበቅ ጌታ ኢየሱስ ጥሩ ምሳሌአችን ነው:: ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው እያወቀ ወደ ንስሃ እንዲመለስ እድል ሰጥቶት ነበር:: በእድሉ አልተጠቀመም እንጂ:: እርግጠኛ ሆነን መናገር የምንችለው ነገር ቢኖር ፍቅርና ትእግስት ለሌሎች ሰዎች በምናሳይበት ጊዜ አዳዲስ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይመጣሉ::